# የኃያላኑ ቀስት እንደምን ተሰበረ?

**ክፍል አንድ** **2009 ዓ.ም**

**(ዴቭ ዳዊት - Dave Dawit)**

በአንድ ወቅት አይደለም ጦር ተሰብቆበት በሠላም ጊዜ እንኳን በሠገነቱ ላይ ከሠፈሩት ርግቦች ላባ ፍላፃን የሚያበጅ፥ በጓሮው ከበቀለው የዘንባባ ዝንጣፊ የጦር ሶማያ የሚሰራው አማራ፤ ጥቃትን የሚሸከም ትከሻ የሌለው፥ በራሱ ባይሆንለት ልጁን "ደም መላሽ" ብሎ በልጁ ጥቃቱን የሚወጣ አማራ ዛሬ ላይ ጥቃትን አሜን ብሎ መሸከም እንደምን ተለማመደ?የእኛ ያልሆነን የተሸናፊነትንና የተንበርካኪነትን የተገገርነትና የተሳዳጅነትን ቀንበር ለሜንቃችን እንዴት አስተማርነው? ይባስ ብሎ ህልውናችን የቁልቁለት ጉዞውን በአስፈሪ ፍጥነት ሲወርድ እያየን የሚገባንን ያህል ለማድረግ እንዴት ይህ በቂ መነሳሻ /adequate stimulus/ ሊሆነን አልተገባም?

መልሱ በውስጥ እና በውጭ የገጠሙን ተግዳሮቶች /Challenges/ ናቸው የሚል እምነት አለኝ። እነዚህን ውስጣዊ እና ውጫዊ ተግዳሮቶች በትክክል ከለየንና መቅረፍ ከቻልን የአማራ ህዝብ ትግል ፍሬ የማያፈራበት፣ አማራነት ወደ ቀደመ ክብሩ የማይመለስበት፣ አማራዊም የአባቱን ሀገር ግዮናዊውን የአማራ ሀገር የማይመሰርትበት እና የሚመኘውን እንደሰው የመኖር መብቱን የማይጎናፀፍበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም።

**1. ውስጣዊ ተግዳሮቶች /Internal Challenges/፡-** ይህ በመወለድ አማራዊ ከሆኑ ከራሳችን ወገኖች የሚመነጩ ተግዳሮቶችን ያካትታል።

**ሀ. የባሮክ እንቅልፍ /Change Blindness/፡-**

በቅዱስ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን በእስራኤል የታሪክ ድርሳናት ውስጥ ከተፃፉት ታሪካዊ ትርክት መካከል የባሮክ ታሪክ አንዱ ነው። ነብዩ ኤርምያስ በነበረበት ዘመን ባሮክ እና አቤሜሌክ የሚባሉ ደቀ-መዛሙርት ነበሩት። ሁለቱም በየዕለቱ ወደ ፈጣሪ ሲፀልዩ "አቤቱ የኢየሩሳሌምን ጥፋት አታሳየን" ይሉ ነበር። ኤርምያስም ከዕለታት በአንዱ ቀን ሁለቱንም ወደ ተለያየ ቦታ ላካቸው።ባሮክ ከተላከበት ቦታ ሲመለስ የፀሐዩ ንዳድ ይበረታበት እና በአንዲት ዛፍ ስር እንደተጠለለ ያሸልበዋል። እግዚአብሔርም በዚያ ባሮክን ለስድሳ ስድስት /66/ ዓመታት በፅኑ እንቅልፍ ጣለው። ነገር ግን ባሮክ ባሸለበባት በዚያች ቅፅበት የባቢሎን ወታደሮች የኢየሩሳሌምን ቅጥር አፈራርሰው በመግባት ነብዩ ኤርምያስን ጨምሮ እስራኤላውያንን በሙሉ በግዞት ወደ ባቢሎን ወሰዷቸው።

ፀሎቱ ሰምሮለት የኢየሩሳሌምን ጥፋት ያላየው ባሮክ ከረጅም እንቅልፉ እንደተነሳ ለ66 ዓመታት መተኛቱን ስለማያውቅ፤ ለውጡንም ስላልተረዳ ያኔ የሚያውቀውን የኢየሩሳሌም መንገድ መፈለግ ጀመረ። ፈልጎም ስላላገኘ ግራ ተጋብቶ እያለ አንድ ሽማግሌ ሰው ያገኝና የኢየሩሳሌም መንገድ በየት ነው? ብሎ ሲጠይቅ ያ አረጋዊ ሰውም "ኢየሩሳሌም በጠፋች በስድሳ ስድስት አመቷ የኢየሩሳሌምን መንገድ ትጠይቀኛለህን?" አለው።

እኛም ዛሬ እንዲህ እንላለን፡- ከረጅሙ እንቅልፍህ ነቅተህ "ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነት፣ አንድነት..." የምትል አማራዊ ለውጡን አስተውል! ኢትዮጵያ ከጠፋች ዘመናት አልፈዋል። የሸዋ መኳንንት የምኒልክን ሞት ምስጢር አድርገውት አመቺ ጊዜ ሲመጣ ይፋ እንዳደረጉት ሁሉ ወያኔም ኢትዮጵያ የምትላትን ሞቷን በአዋጅ ሊነግርህ አመቺ ጊዜ ብቻ ነው የሚጠብቀው። እንደ ኖህ ዘመን ሰው የጥፋት ውሃ መዝነብ ሲጀምር ነው መርከብ መስራት የምጀምር አትበል። መርከብህ የሆነውን ግዮናዊውን የአባትህን የአማራን ሀገር ለመስራት መነሳት ያለብህ ዛሬ ነው። ኖህ ከጥፋት ውሃ የዳነው መዝነብ ከመጀመሩ በፊት መርከቡን ቀድሞ ስላዘጋጀ ብቻ ነው።

አንድ ስሩ ተቆርጦ የሞተንና የደረቀን ዛፍ አርቲፊሻል ቅጠልና አበባ ብታለብሰው ከሩቅ ለሚያየው ሰው ዛፉ በህይወት ያለ ሊመስለው ይችላል። የዛሬዋ ኢትዮጵያም እንዲሁ ወያኔ ጊዜ ለመግዣ ባለበሳት አርቲፊሻል ቅጠልና አበባ በህይወት ያለች ብትመስልም ዳሩ ከሞተች ዘመናት አልፈዋል። ለመሞቷም ያንተ እጅ ስለሌለበት፡-

"ይሆናል ብለን ወፍ አጠመድን፥
ሳይሆን ሲቀር ግን ፈተን ለቀቅን።"

ብለህ ወደ ወገኖችህ ተመልከት። የሞተችውን ኢትዮጵያ በህይወት እንዳለች አስመስሎ በራሱ ምናብ የሚቃኘውን የአማራ ተወላጅም ከሰማህ አንቃው አለበለዚያ ግን ሎጥ ወደ ምትጠፋው ሰዶም እና ገሞራ ዞሮ እንዳላየ ሁሉ አንተም የቅዠቱ ተካፋይ ላለመሆን ዞረህ ሳታይ ሊመጣ ካለው መከራ ለመትረፍ ወደ ተስፋ ምድርህ ወደ ግዮናዊው የአባትህ ሀገር ምስረታ ተሰብሰብ።

## ለ. የሹላማይቷ ሴት ምላሽ /Bystander Effect/፡-

ጠቢቡ ሰሎሞን ከፃፋቸው መጽሐፎች መካከል በአንዱ ውስጥ የሹላማይቷ ሴትና የወዳጇ ታሪክ ይገኝበታል። የሌሊቱ ግርማ በሚያስፈራ፣ ጠል በሚወርድበት በዚያ ምሽት ሹላማይቷ ሴት በአልጋዋ ላይ ነበረች፤ እንቅልፍ ግን አልወሰዳትም። ካስፈሪው ጨለማ፣ከሚወርደውም ጠል ለመጠለል ወዳጅዋ የሆነው ሰው የቤቷን መዝጊያ እያንኳኳ ልብን በሚነካ ቃል "እኅቴ፥ ወዳጄ፥ ርግቤ፥ መደምደሚያዬ ሆይ፥ በራሴ ጠል፥ በፀጉሬም የሌሊት ነጠብጣብ ሞልቶበታልና ክፈችልኝ። " እያለ ሲማፀናት ከወዳጅ የማይጠበቀውን ምላሽ እንዲህ ስትል ትመልስለታለች፡- "ቀሚሴን አወለቅሁ፤ እንዴት እለብሰዋለሁ? እግሬን ታጠብሁ፤ እንዴት አሳድፈዋለሁ?"

ተልካሻ ምክንያት እየደረደረች እንደማትከፍትለት ያወቀው ሰውም ራሱን ለማትረፍ ሲል እጁን በበሩ ቀዳዳ አሾልኮ ለመክፈት ሞከረ፤ አልሆንለት ሲልም ተስፋ ቆርጦ ሄደ። እሷም ጅብ ከሄደ ውሻ... እንደሚባለው እንዲህ ትላለች "አንጀቴም ስለ እርሱ ታወከ። ለውዴ እከፍትለት ዘንድ ተነሣሁ፥ ውዴ ግን ሄዶ ነበር። ነፍሴ ከልመናው ቃል የተነሳ ደነገጠች፤ፈለግሁት፥ አላገኘሁትም፤ ጠራሁት አልመለሰልኝም። ከተማይቱን የሚዞሩ ጠባቂዎች አገኙኝ፤ መቱኝ፥ አቆሰሉኝም......" እያለች ከረፈደ በኋላ ነገሮችን ለማስተካከል ስትሞክር አልሰምር እያለ እንዴት ዋጋ እንዳስከፈላት ትናገራለች።

አማራዊ ሆይ! ዛሬ ወገንህ አማራ በመሆኑ ብቻ የቀን ጨለማ ውጦት፤ የመከራ ዶፍ እየወረደበት አንተ ልጁ ከሚያሳድዱት እንድታስጥለው መሸሸጊያ ቤቱን እንድትከፍትለት በደጅ ቆሞ እየተማፀነህ ነው። ዛሬ ልትደርስለት ሲገባ "ቀሚሴን እንዴት እለብሳለሁ?፤ እግሬንስ እንዴት አሳድፋለሁ?" በሚል ተልካሻ ምክንያት የወገንህን ሰቆቃ ችላ ብትል ዛሬ ወገንህን እያጠፉ ያሉት ነገ አንተንው እንደ ሹላማይቷ ሴት ያጠፉሃል።

አማራዊ የሆንክ የወገንህ ጥቃት ያንተም ጥቃት ነው። ከዳር ሆነህ በወገንህ አጥንት እና ስጋ እየነደደ ያለውን እሳት የምትሞቅበት ወቅት ማብቂያው አሁን ነው። ከዳር ሆነን የምናይበት ጊዜ ሊያበቃ ግድ ነው። አንዱ አማራዊ ስለሁሉ አማራዊ፥ ሁሉ አማራዊም ስለ አንዱ አማራዊ የሚቆምበት ጊዜ ዛሬ ነው። በአማራዊነትህ ተነስ፥ የወገንህ ጥቃት ያስቆጣህ!

## ሐ. ራስን አግዝፎ የማየት አባዜ /Delusion of Grandeur/፡-

ባለፈው ሰሞን አንድ የዳያስፖራ ቴሌቪዥን ጣቢያ በአማራ ጉዳይ የሚሰሩ ግለሰብን ቃለ-ምልልስ ሲያደርግ እያየሁ ነበር። እናም ጋዜጠኛው "ለምንድነው አማራ የራሱን ሀገር መመስረት አለበት የምትሉት?፤ ከትግሬ ውጪ ሁሉም አማራን ይፈልገዋል እንዲያውም ደቡብ እኮ አማርኛ ቋንቋን ነው የሚጠቀም" እያለ ጉንጭ አልፋ ክርክር ሲያደርግ ሳይ ምርጫ 97 ነው ወደ አዕምሮዬ የመጣው። በምርጫው ማግስት ቅንጅት የሚባለው ድርጅት ፓርላማ እንግባ አንግባ እያለ ሲወራከብ ህብረት የሚባለው ድርጅት ሊቀመንበር የሀድያ ተወላጁ በየነ ጴጥሮስ በአ.አ ዩኒቨርሲቲ መምህር የነበረውን ዶክተር ተጠምቀ የተባለውን ትግሬ ከስዩም መስፍን ጋር ካላገናኘኸኝ ሞቼ እገኛለሁ ይለዋል። ዶክተሩም አገናኘው።በየነስ ስዩምን ምን አለው?

"ስልጣናችሁን ለአማራ አሳልፋችሁ እንዳትሰጡ፤እኔ መረራን አሳምኜ ህብረት ፓርላማ እንዲገባ አደርጋለሁ።" አለ። አደረገውም። እንግዲህ ኦሮሞዎቹ ብርትኳን ሚደቅሳ፣ ዶ/ር አድማሱ እና በግማሽ ሀይሉ ሻውል፤ ጉራጌዎቹ ዶ/ር ያዕቆብ እና ብርሃኑ ነጋ፤ ትግሬው ኃይሉ አርአያ በበላይነት የሚመሩትን ቅንጅትን ነው እንግዲህ በየነ አማራ እንዳይመጣብን ብሎ አቧራ ያስነሳው።

እውነት ደቡቡ አማራን የሚፈልግ ቢሆን ገፍፎ እና ዘርፎ ከወያኔ ጋር በማበር ከክልሉ ያባርረው ነበር? ይህ "ሌሎች ይወዱኛል፤ ሌሎች ይፈልጉኛል" የሚል አባዜ ስር የሰደደ ችግር እንጂ የአንድ ጋዜጠኛ ችግር ብቻ አድርገን አንውሰደው። አማራዊ የሆንክ ከእንደዚህ አይነት የቀን ቅዠት ውጣ!ካንተ ከአማራዊ ወገንህ ውጪ ማንም አይፈልግህም። ሊፈልግህ ቢችል እንኳ በሁለት እግርህ ራስህን ችለህ ስትቆም እንጂ ዛሬ ዛፍ እንዳጣ አሞራ እየተቅበዘበዝክ፣ እየተሳደድክ እና በየጎዳናው እየታደንክ ባለህበት ሁኔታ አይደለም። አማራዊ ሆይ በመጀመሪያ ራስህን አድን፣ ቤትህን ስራ ማረፍያህን አዘጋጅ። ላለፉት ሃያ ስድስት አመታት ያሳለፍከው የመከራ ተሞክሮ የሚያሳይህ ሌሎች በቁስልህ ላይ ጥዝጣዜን ሲጨምሩብህ እንጂ ቁስልህን የሚጠርግ አንድም ሳምራዊ አላገኘህም። "ሌሎች ይወዱናል፤ሌሎች ይፈልጉናል" በሚል የቀን ቅዠት የሚዋልለውን ወገንህን በተቻለህ መጠን አንቃው፥ መራራውን እውነት እንዲያይ እርዳው። አሻፈረኝ ካለህ ግን ራስህን ለይ እና ወደ አማራዊ ወገኖችህ፥ወደ ወጣህበት መንጋ ተቀላቀል።

**መ. ራስን መካድ /Self-Denial/:-**

አንድ የወይን እርሻ የነበረው ሰው ነበረ። እንዲህም አደረገ "በዙሪያው ቆፈረ፥ ድንጋዮችንም ለቅሞ አወጣ፥ ምርጥ የሆነውንም የወይን ሐረግ ተከለበት፥ በመካከሉም ማማ ሰራ፥ ደግሞም የመጥመቂያ ጉድጓድ ማሰበት፤ ወይንንም ያፈራ ዘንድ ተማመነ፥ዳሩ ግን ሆምጣጣ ፍሬ አፈራ።"

ትናትናም ይሁን ዛሬ አማራዊ አባት ልክ እንደ የወይን እርሻው ባለቤት ሁሉን አድጎላቸው ከፍ ካለ ማማ ላይ የሰቀሏቸው ልጆቹ በምላሹ ጣፋጭ ወይንን ከማፍራት ይልቅ ራስን በሚያስክድ አባዜ ተጠልፈው መራራን ነገር ሲያፈሩ ታዝበናል፤እየታዘብንም ነው።

ትናንት የአማራ ህዝብ እረኛ እንደሌለው መንጋ በማንም ተኩላ እየተነጠቀ እየታረደ በነበረበት ወቅት ጥቃትህ ጥቃቴ ነው ብሎ እንደምሁር መንጋውን መምራትና ማደራጀት ሲገባው "ጥናት አጥንቼ ደረስኩበት" ባለው ሸውራራ ዕውቀቱ እየተገፋ "አማራ የሚባል ነገር የለም" እያለ የአራጆቻችንን ቢላ ሲስል አይተናል። ትናንት ትግሬ ተራብ ብሎ አኮፋዳ ሸክፎ በየሀገሩ እየዞረ ደጅ እንዳልጠናላቸው በምርጫ 97 ማግስት መምህር ገብረኪዳን ደስታ የሚባለው የትግሬ ፀሐፊ በአማርኛ ባሳተመው ፀረ-አማራ መጽሐፉ ላይ በፕሮፌሰሩ ላይ እንዲህ እያለ ነበር መርዷቸውን ያረዳቸው "ሂትለር ከአይሁዳዊት ሴት ልጆች ቢወልድ የአይሁዶች ለሂትለር ያላቸው አመለካከት እንደማይቀየር ሁሉ፤ ፕሮፌሰር መስፍን ከትግራይ ሴት ልጆች ስለወለደ ጠላቱን ጠንቅቆ የሚያውቀው የትግራይ ህዝብ ለፕሮፌሰሩ ያለውን አመለካከት አይቀይርም።" ነበር ያለው።

ዛሬም የፕሮፌሰሩ መንፈስ የተጠናወታቸው ራሳቸውን የካዱ አማራውያን በሚዲያዎቻቸው አማራ ተፈናቀለ ከማለት ይልቅ "አማርኛ ተናጋሪ ህዝቦች ተፈናቀሉ" ይላሉ። የአማራ ታጋዮች ከማለት ይልቅ "የነፃነት ኃይሎች" ይላሉ።

እስኪ የሚሉትን በሌላ ምሳሌ እንየው። የራሽያ ቋንቋ ሩስኪ ይባላል። ይህን ቋንቋ ከራሽያ ጀምሮ የማዕከላዊ ኤዥያ ሀገራት የሆኑት ካዛኪስታን፣ ኡዝቤክስታን፣ ቱርክሜንስታን፣ ታጃኪስታን፣ ኪርጊስታን እንዲሁም የካውካሰስ ሀገራት የሆኑት አዘርባይጃን፣ ጆርጂያ እና አርሜንያ ወደ ላይ ደግሞ የቦልቲክ ሀገራት የሆኑት ሌቲቪያ፣ ኢስቶንያ፣ ሉቶንያ እና ቤላሩስ እንዲሁም የምስራቅ አውሮፓዎቹ ሞልዶቫ እና ዩክሬን ይናገሩታል። ይባስ ብሎም ግማሽ የሚሆነው የእስራኤል ህዝብ ከእነዚህ ሀገራት ወደ እስራኤል የተመለሰ በመሆኑ ሩስኪን አቀላጥፎ ልክ እንደራሻዎቹ ይናገራል። ታድያ አንዱ ተነስቶ ፑቲን ሩስኪ ተናጋሪ ህዝቦችን እየበደለ ነው ቢል ምን ትርጉም ይሰጣችኋል? ትርጉም የሚኖረው ፑቲን የራሽያ ህዝብን እየበደለ ነው ቢባል ነው። ምክንያቱም ሩስኪ የሚናገሩ ህዝቦች ሁሉ በፑቲን አስተዳደር ስር ያሉ ስላልሆኑ። በአማራ ህዝብ እና በአማርኛ ተናጋሪ መካከልም ያለው ልዩነት እንዲሁ ነው። አማራዊ ዜጎቻችን ሲበደሉ የአማራ ህዝብ ብሎ ከማለት ይልቅ አማርኛ ተናጋሪ ህዝቦች

እያሉ የሚያናፍሱ የራሳችን ሰዎች በህዝባችን ላይ ተደጋጋሚ ክህደትን እየፈፀሙ እንዳለ ሊታወቅ ይገባል። አማራዊ የሆንክ ወገናችን! ሌላውን አስደስታለሁ ወይ እጠቅማለሁ ብለህ ራስህንና ወገንህን ክደህ ስለሌላው ብትሞት፣ አይደለም ቆዳ ተሸክመህ ለጠኔያቸው ማስታገሻ ምግብ መለመን ቀርቶ ቆዳህን እንኳን ገፈህ ብታነጥፍላቸው ላንተ ያላቸው ጥላቻ እና ንቀት መቼውንም አይቀየርም።መቼውንም!!!

ፕሮፌሰሩ በትግሬ ህዝብ ዘንድ እንደባለውለተኛ ሊመሰገኑ ሲገባ ከሂትለር ጋር እንዴት እንዳመሳሰሏቸው ትምህርት ይሁንህ። አበበ ገላው የሚባለው ጋዜጠኛ /አማራ ማለት ከብዶት አማርኛ ተናጋሪ፣ የነፃነት ኃይሎች የሚለውን ተቋም በበላይነት የሚመራው/ ጃዋርን አጋር ያደረገ መስሎት ሚኒሶታ ድረስ ሄዶ እጆቹን እያመሳቀለ "ዳዎን ዳዎን ወያኔ" ሲል ቢውልም አመሻሹ ላይ ጃዋር በራሱ ቋንቋ አበበን እንዴት በማጅራቱ በኩል እንዳረደው ትምህርት ይሁንህ። ገንዘብህን፣ ዕውቀትህን፣ጊዜህን ለአማራ እና ለአማራ ብቻ አውል!ራስህን አክብር፤ ያንተ የሆነን ነገር ዋጋ ስጠው!ከልጅነት ጀምሮ ወይንን እንድታፈራለት ተንከባክቦ ላሳደገህ አማራዊ ዜጋ ወይን ነህና ጣፋጭ ወይንን አፍራ!!!

### ሠ. የኤማሁስ መንገደኞች /Day-Dreamers/፦

ክርስቶስ ከሞት በተነሳበት ዕለት እንዲህ ሆነ። ከተከታዮቹ ሁለቱ ከኢየሩሳሌም አቅራቢያ ወደምትገኝ ኤማሁስ ወደምትባል ስፍራ መንገድ ጀመሩ። ክርስቶስም ሌላ መንገደኛ መስሎ ቀረባቸው እና የሚያወሩትን ሲሰማ ስለምን እንደሚናገሩ ጠየቃቸው። እነሱም ስለሱ የሆነበትን ሁሉ ከነገሩት በኋላ ለዚህ ርዕስ የሚስማማውን ነገር ተናገሩ፦ "እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዥ ያለው እርሱ እንደሆነ ተስፋ አድርገን ነበር፤.... ።"

ያሉትን ነገር ይበልጥ ግልጽ ላድርገውና በወቅቱ እስራኤል መንግስቷ ፈርሶ በሮማውያን ቅኝ ተይዛ ነበር።እናም እነሱ የሚያስቡት ሮማውያንን አባሮላቸው እስራኤልን ነፃ ሀገር እንዲያደርግላቸው ነበር። ፈጣሪ ያሳያችሁ ሰላሳ ሶስት ዓመት ሙሉ ስለ ሰማያዊው የእግዚአብሔር መንግስት እና ለመንፈሳዊ ተልዕኮ እንጂ ምድራዊ የሆነውን ስራ ለመስራት እንዳልመጣ ሲያስተምራቸው ቢኖርም የነሱ ሃሳብ እና ፍላጎት ግን ሌላ ዓለም ውስጥ ነበር ያለው።

ይህ እጅና እግርን አጣምሮ ፈጣሪ ያደርገዋል የሚል አመለካከት በእስራኤላውያኑ ዘንድ ስር የሰደደ ችግር ስለነበር ለ ሁለት ሺህ አመታት ሀገር አልባ ሆነው እንዲንከራተቱ አድርጓቸዋል። ነገር ግን በ1897 ዓ.ም. የጽዮናውያን እንቅስቃሴን ሲጀምሩ ፈጣሪም ረድቷቸው 50 ዓመት በሆነ ጊዜ ውስጥ መንግስት መመስረት ቻሉ።

እኔ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን እንደሆንኩት ሁሉ ሌላው አማራዊም የሚፈልገውን እምነት ቢከተል ችግር የለውም።ነገር ግን የራሳችንን የስራ ድርሻ ዘንግተን ፈጣሪ እንዲያከናውንልን መጠበቅ ፍፁም ስህተት ነው።

ውሃውን በበትር የመታው ሙሴ ነው፤ለሰው የማይቻለውን ባህሩን የከፈለው ግን ፈጣሪ ነው። የአልዓዛርን የመቃብር ድንጋይ ሰዎች እንዲያነሱት ነው የተደረገው፤ለሰው የማይቻለውን አልዓዛርን ከሞት ያስነሳው ግን ክርስቶስ ነው። እኛ የራሳችንን ድርሻ ማንሳት ከቻልን የማንም ዕንባ ባለዕዳ ያልሆነው ፈጣሪያችን በነፃነት እንድንኖር ለምናደርገው የነፃነት ትግል እንደሚረዳን ምንም ጥርጣሬ ሊገባን አይገባም።

የአማራ ህዝብ የሞራል ልዕልና እንዲኖረው ካስቻሉት ነገሮች አንዱ እምነት ያለው ህዝብ መሆኑ ነው። ነገር ግን እስራኤላውያን ለሁለት ሺህ አመታት የሰሩትን ስህተት ላለመድገም ቀን ከሌሊት ከእኛ የሚጠበቀውን ማድረግ እና የድርሻችንን ማንሳት ይኖርብናል።

### ረ. የዋለልኝ ፍሬዎች /Self-hate Amharas/፦

"ስም ይወጣል ከቤት፥ ይቀበላል ጎረቤት" የሚል በሳል ብሂል አለን። "የኢትዮጵያ አብዮት " እየተባለ በሚጠራው የስልሳዎቹ ትውልድ ውስጥ ዋለልኝ መኮንን የተባለው ራስ-ጠል አማራ በኢትዮጵያ ውስጥ የብሄር ጭቆናና የአማራ የበላይነት እንዳለ

በማስመሰል ያሰራጨው መርዛማ ጽሑፍ ዛሬ ድረስ ለዘለቀው አማራንና አማራዊን ለማጠልሸት መሠረት የጣለ ነበር።መጽሐፍ የዋለልኝ አይነቱን ወገኑን የሚጠላውን "አባቱን የገደለ፤ እናቱን ያገባ፤ ጌታውን የሸጠ የጥፋት ልጅ " ይለዋል። ዛሬም የዋለልኝ ፍሬዎች በማህበረሰባችን ውስጥ ተሰግስገው ጠላት ከሚወጋን በላይ ትልቅ ጥፋት በህዝባችን ላይ እየፈጸሙ ይገኛል።

ትናንት ሶማሌው አማራዊውን እንዲገድለው ሲቀሰቅስ የነበረው የትናንቱ ጠቅላይ ሚንስቴር የዛሬው ፓስተር ነኝ ባይ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።

ትናንት የገዛ ወገኑ ተገፎ እና ተዘርፎ ሲባረር ሳያሳስበው "እንዳይባረር የትምክህት ለሀጩን መጥረግ አለበት"፣" አማራ በባዶ እግሩ እየሄደ....." እያለ በቁስላችን ላይ እንጨት የሰደደው አለምነው መኮንንም የበጣም ቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ከሰሞኑ ደግሞ በኖርዌይ እሱና ቤተሰቦቹ በመንግስት ዌልፌር እየተጦረ የሚኖር ዶክተር ነኝ ባይ በአማራ ሀገር ምስረታ ዙሪያ የሚሰሩትን "የአማራ አነጎች" እያለ የጭቃ ጅራፉን ሲያጮህ ሰምተናል። እርግጥ ነው ቀበቶውን አላልቶ ቀፈቱ እስኪሞላ የዌልፌር ምግብ ሲበላ የኖረን ሰው የወገኑን ጥቃት ለማስቆም እጅጌህን ሰብስብ፥ ቀበቶህንም አጥብቅ መባልን አይሻም።

"ውሃን ምን ያስጮኸዋል? ቢሉ፥ በውስጡ ያለው ድንጋይ" ይባል የለ!
አማራዊ ሆይ! በሥነ-ቃልህ ውስጥ፡-
"ጠላትማ ምንጊዜም ጠላት ነው፤

አስቀድሞ ማለት አሾክሿኪውን ነው።" የሚል አባባል አለህ። ስለሆነም ከአብራክህ ወጥቶ፥ ማዕድህን በልቶ ካደገ በኋላ ከጠላቶችህ ጋር የሚጠላህን፣ መንገድ መሪ ሆኖ ጥፋትህን የሚያፋጥነውን እሱን አስቀድመህ አጥፋው። ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ህይወት ሁሉ አግልለው። በሀዘኑም በደስታውም አትካፈል፤ በሀዘንህ እና በደስታህም እንዲካፈል አትፍቀድለት።

እንግዲህ የውስጥ ተግዳሮቶችን ያየንበትን የዛሬውን ፅሑፍ በዚህ እንቋጭ። በቀጣይ ውጫዊ ተግዳሮቶችን እና መደምደሚያውን እናያለን።

እግዚአብሔር ግዮናዊውን የአማራ ሀገር ይባርክ!!!አሜን።

**የኃያላኑ ቀስት እንደምን ተሰበረ?**

**/ክፍል ሁለት/**

### ሰ. የሰመርናሃ ሰፋሪዎች /The Amhara Elites/:-

እንዲህም ሆነ። እስራኤል በባቢሎን ለሰባ ዓመታት በባርነት ከሚኖርበት ግዞት ሊወጣ ሲቃረብ ነብዩ ኤርምያስ እስራኤላውያን ጣዖትን ከሚያመልኩ ባቢሎናውያን ጋር ጋብቻን እንዳይፈፅሙ፤ የፈፀሙትም እንዲያፈርሱ ያስተምር ነበር። ጣዖት አምላኪዎች ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገቡ የተከለከለ ነበርና። ጊዜው ደርሶ እስራኤል ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ ኤርምያስና የጎበዝ አለቆቹ በኢየሩሳሌም በር ቆመው ከባቢሎናውያን ጋር የተጋቡትን እንዳይገቡ ከለከሏቸው። ከባቢሎንም ከኢየሩሳሌምም የተባረሩት እነዚህ ሀገር አልባ ሰዎች እግራቸው ወደመራቸው ሲጓዙ አንድ ስፍራ አገኙ። በዚያም ሰፈሩ። የቦታውንም ስም

"ሰመርናሃ" ብለው ጠሩት፥ በኋላም ያ ስፍራ ሰማርያ ተባለ። የሰማርያ ሰዎች በወገኖቻቸው ላይ ክህደትን ፈጽመዋልና፤በባርነት ካስገበሯቸው ባቢሎናውያን ጋር ተዛምደዋልና ከጣኦት አምላኪዎች ጋርም ተጋብተዋልና በአይሁድ ዘንድ እጅግ የተናቁ ነበሩ።

ዛሬም እንዲሁ ለቁጥር አታካች የሆነው የአማራ ልሂቅ "አንድነት" ከምትባል ወገኖቻችንን በግፍ እንዲጨፈጨፉ ምክንያት ከሆነች ጋለሞታ ጋር በቀላሉ የማይፋቱት ጋብቻ ፈፅመው የእነሱ አቻ የሆኑቱ የሌሎች ብሄሮች ልሂቃን ጊዜያቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ገንዘባቸውን ለወገኖቻቸው ከማዋል አልፈው በመሰሪ ተግባራቸው አማራዊ ወገኖቻችንን ለማጥፋት ሲጠቀሙበት የእኛዎቹ ግን ለራሳቸው ሀገር አልባ፥ ለወገናቸው ዕዳ፥ ለትውልዱም ማፈሪያ ሆነዋል። በዚህም ምክንያት አማራዊ ወገናችን እንዳልወለደ፣ እንዳላስተማረ፣ "እደጉ፥ ተመንደጉልን" ብሎ እንዳልደገፈ ሁሉ የወላድ መካን ሆኖ ሲሳደድ እና ሲገደል፣በግፍ ከነነብሱ በቀበሮዎች ጉድጓድ ሲቀበር፣ ማረፊያ አጥቶ ሲቅበዘበዝና የሰው ልጅ ይሸከመዋል ተብሎ የማይታሰብ ግፍ እና መከራ ሲደርስበት የአማራ ልሂቃኑ ግን ወያኔ ከዘመናት በፊት የገደላትን ኢትዮጵያ የሙት መንፈሷን ጣዖት በማምለክ፥ እንዲሁም የአመንዝራይቱ ኤልዛቤል ምሳሌ ከሆነችው ከ"አንድነት" ጭን ውስጥ መውጣት ባለመቻላቸው ህዝባችን ለባህርይው የማይስማማውን ጥቃት እና በደልን እንዲሸከም ትልቅ አስተዋፆ አበርክተዋል።

ዶክተር መረራ ጉዲና "የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምስቅልቅል ጉዞና የህይወቴ ትዝታዎች (ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ እስከ ኢህአዴግ)" በተሰኘ መፅሀፉ የሌሎች ብሄር ልሂቃን በአማራ ልሂቃን ላይ ሁለት ጊዜ ክህደት እንደፈፀሙበት ይጠቅሳል። በ66ቱ አብዮት ማግስት እና በደርግ ውድቀት ማግስት ማለት ነው። በነዚህ ሁለት ወሳኝ ወቅቶች የሌሎች ብሄር ልሂቃን "አጥብቀህ ጎርሰህ፥ ወደ ወገንህ ሩጥ" የሚለውን ብሂል ተግባራዊ ሲያደርጉ የአማራ ልሂቅ ግን ከባቢሎንም ከኢየሩሳሌምም ሳይሆን እንደውሃ ላይ ኩበት ሲዋልል መሠረቱ የሆነውን የገዛ ወገኑን ለፈፅሞ ጥፋት እንዲጋለጥ አድርጓል።በእኔ እይታ በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የአማራ ልሂቅ በአራት መጥፎ እና አደገኛ ምድብ ውስጥ ተከፍሎ ይገኛል።

## 1ኛ. ክህደት ምሱ /The Ignorant Elites/፡-

"ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል?"

በእንግሊዝኛ አንድ አባባል አለ "Fool me once, shame on you; fool me twice, shame on me!" እውነት ነው! ማንነትህን አስቀድሜ ላውቀው ባለመቻሌ ለመጀመሪያ ጊዜ ብታታልለኝ ቅሌታሙ አንተ ነህ! ለሁለተኛ ጊዜ እንድታታልለኝ ከፈቀድኩልህ ግን በእርግጥም ቂሉ እኔ ነኝ።

አማራዊ ልሂቅ ሆይ! ከአንዴም ሁለት ጊዜ አንተ "አንድነት"፣ "ኢትዮጵያ" እያልክ አብዝተህ ስትጣራ ለጊዜው ካንተ ጋር የቆሙ የመሰሉህ፥ በመጨረሻው ግን አጥብቀው ከፊትህ ሸሽተው አንተን እና የወጣህበትን አማራዊ ወገንህን በጠላትነት በመፈረጅ ክህደት ፈፅመውብሃል፤ ወገንህን ካላጠፉ ዕረፍት ላያገኙ ተማምለውም ዳግም ከደውሃል።

ከሃዲዎች በመጀመሪያው ክህደት አንተን እና አማራዊ ወገንህን በጠላትነት ፈረጁ። በሁለተኛው ክህደት የህዝብህን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መሠረቱን ንደው የቻሉትን ገድለው ያልቻሉትን አሳደው ካሉት በታች፥ከሞቱት በላይ ሆኖ እንዲቅበዘበዝ አደረጉት። ዛሬ ራስህን ለሦስተኛ ክህደት ካመቻችህላቸው አንተንም ሆነ የወጣህበትን ህዝብህን እንደ ነጣቂ መብረቅ፥እንደ ተራበም ተኩላ ሊናጠቁህ ፈፅሞም ሊያጠፉህ አሰፍስፈዋል።

ታዲያ ከሃዲዎቹ እንደ ጴጥሮስ ከሶስት ጊዜ ክህደት በኋላ በንሰሐ ይመለሳሉ ከሚል የቂል ምኞት ማማ ላይ ራስህን ሰቅለህ እስከመቼ ትኖራለህ? ያንተ ስህተት እኮ ዕንቁዎችህን በእሪያዎች መካከል ማኖርህ ነው። ያንተ ስህተት ውሾቹ ቅዱሱን በእግራቸው እንዲረግጡት፥ ተመልሰውም እንዲነክሱህ የተቀደሰውን ነገር ለውሾች መስጠትህ ነው። ዛሬ ግን በቃ ልትል ግድ ይላል።

አንተ እኮ በተፈጥሮህ አልጫውን የምታጣፍጥ ጨው ነበርክ። ከሃዲዎች ድንጋይ ነው ብለው ወደ ውጪ የጣሉህ የወጣህበትን አማራዊ ወገንህን ትተህ፥ ያለተፈጥሮህ አልጫ ሆነህ ስለተገኘህ ብቻ ነው። አንተ እኮ በተፈጥሮህ ጨለማን የምትገላልጥ ብርሃን

ነበርክ። በአማራነት መቅረዝ ላይ ከፍ ብለህ ልታበራ የተፈጠርክ ብርሃን እንጂ ከሃዲዎች እንቅብ የሚደፉብህ የጋን ውስጥ መብራት አልነበርክም። ከማንነትህ ጋር የምትታረቅበት፣ ወደ አባትህ ቤት የምትመለስበት፣ ለአማራዊው ወገንህም ጋሻ ሆነህ የምትቆምበት ጊዜ ዛሬ ነው።

አንተ የተኛህ አማራዊ ልሂቅ ንቃ!!! እንደ አቻዎችህ አንተም ዕውቀትህን፣ ጊዜህን እና ገንዘብህን ለአማራዊ ወገንህ አውል!!! ወትሮም ኮትኩቶ ዛሬ ለደረስክበት ዕልቅና ያደረሰህ አማራዊ ወገንህ ነው፤ ደግሞም መደበቂያ የሚሆንህ ከጥፋትም የምትድንበት የመሸሸጊያ ምድርህ ይኸው የአባትህ ርስት ግዮናዊው የአማራ ሀገርህ እንጂ ከሃዲዎቹ ያፈረሷት እና ከአዕምሮህ አልጠፋ ያለችው የምናብህ ኢትዮጵያ አይደለችም።

## 2ኛ. የይሁዳ ፍየሎች /The Judas goat/

የይሁዳ ፍየል ማለት በተለይ በምዕራቡ ዓለም ከብት አርቢው ከመንጋው መካከል አንዱን ፍየል ነጥሎ ይወስደውና ሌሎቹን ፍየሎች ወይም በጎች ሳይበታተኑ ከፊት ከፊት እየመራ ባለቤቱ ወደሚፈልግበት ቦታ እንዲወስዳቸው ያሰለጥነዋል። አብዛኛውን ጊዜ የይሁዳ ፍየል መንጋውን እየነዳ የሚወስደው የበጎቹ ፀጉር ወደሚሸለትበት ቦታ አልያም በጎቹ ወደሚታረዱበት ስፍራ ሲሆን የይሁዳው ፍየል ራሱን ከመንጋው ጋር በማመሳሰል ተራ በተራ መንጋውን ወደመታረድ እየመራ የደም ምንዳ ይሰፈርለታል።

እንዲሁ ዛሬ ከአማራ ልሂቃኑ መካከል ጥቂት የማይባሉት አፋቸው ከእኛ፥ ልባቸው ግን ከእነኛ ሆኖ አንድ የሆነውን የአማራን ህዝብ አራጆቻችን በሚፈልጉት መልክ በመንጋ በመንጋ እየከፋፈሉ እና ከፊት ሆነው እየመሩ ለሸላቶች እና አራጆች ቢላ እያመቻቹን ይገኛሉ።

መለስ ዜናዊ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ 2010 ዓ.ም. በፓርላማ ተገኝቶ ከደቡብ ክልል በግፍ ስለተፈናቀሉት አማራውያን ቃል በቃል እንዲህ ነበር ያለው "አማራ ተፈናቀለ እየተባለ የሚባለው መሠረት የሌለው ነው። እነዚህ ሰዎች የምስራቅ ጎጃም ሰዎች ናቸው። በሞፈር ዘመት ሄደው የሰፈሩ የምስራቅ ጎጃም ሰዎች ናቸው……………።" መለስ የሚናገረውን የማያውቅ ሰው ሆኖ አይደለም "አማራ ሳይሆኑ ሞፈር ዘመት የምስራቅ ጎጃም ሰዎች ናቸው" ያለው በወቅቱ ቢሳካለት ሌላው አማራ የተሰደዱትን ሰዎች የምስራቅ ጎጃም ሰዎች እንጂ የእኔ አካባቢ ሰዎች አይደሉም ብሎ እንዲያስብለት ከመመኘት ነው። በተመሳሳይ ዛሬ አማራዊው የአማራ ተወላጅ በመሆኑ ብቻ የግፍ ዶፍ እየወረደበት ሳለ የይሁዳ ፍየሎች ግን ከአሳዳሪዎቻቸው በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት "የጎንደር ህብረት"፣ "የጎጃም ህብረት" እያሉ አማራዊው በአንድ ጥላ ሥር እንዳይሰባሰብ እና የተጋረጠበትን የፈፅሞ መጥፋት አደጋ አንድ ሆኖ እንዳይከላከል ትልቅ ዕንቅፋት ሆነዋል።

አማራዊ ሆይ! ጎጃም፣ ጎንደር፣ ወሎ እና ሸዋ የአንተ ወይም የወላጆችህ የትውልድ ስፍራ እንጂ የአንተ ማንነት አይደለም።አንተ ደምህ አማራ ነው!!! ጥቃት የተከፈተብህ ደምህ አማራዊ ስለሆነ ብቻ ነው!!! ጎጃምም ተወለድ ጎንደር፤ ወሎም ተወለድ ሸዋ ጠላት አንተን የሚያውቅህም ሆነ የሚጠራህ አማራ ብሎ ነው!!! አንተን አማራነትህን አስክዶ በትውልድ ቦታ ሊከፋፍልህ እየሞከረ ያለው የይሁዳ ፍየል አንተን መስሎና አንተን አህሎ በመሳም ለአሳዳጆችህ አሳልፎ ሊሰጥህ የደም ምንዳ ተከፍሎታል። በቁምህ ሽጦህ የደም መሬት አኬልዳማ ገዝቶበታል።

አማራዊ ሆይ! አንተ እኮ ትልቅ ህዝብ ነህ። አንተ እኮ በህግ የተወለድክ የእመቤቲቱ የሳራ /የጣይቱ/ ልጅ ነህ። ያለህግ የተወለደው የገረዲቱ አጋር ልጅ ፥ ያ ከሃዲ በትውልድ ስፍራ ሊከፋፍልህ ሲነሳ፤ ከጠላትህ ጋር በምስጢር ወግኖ ሊያጠፋህ ሲያደባ አንተም በምላሹ "በቃ! ገና ከበለስ በታች ሳለህ የይሁዳ ፍየል መሆንህን አወቅሁ" ልትለው ይገባል። እናንት የአማራ ልጆች! ጠላት አንድ የሆነውን የአማራን ህዝብ በትውልድ ስፍራ ከፋፍሎ ለማጥፋት ያመቻቸው ዘንድ በይሁዳ ፍየሎች ፊታውራሪነት ያዘጋጃቸውን "የጎንደር ህብረት"፣ "የጎጃም ህብረት" የሚባሉ የጠላት የመውጊያ ዘንጎችን ሰባብሩ!!! ንሑሩሽታን /ሰባብሩት/!!!

## 3ኛ. የሌሊት ወፎች /The Tepid-Water Effect/

"በራድ ወይም ትኩስ እንዳልሆንክ ስራህን አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር። እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንክ ከአፌ ልተፋህ ነው።" የሌሊት ወፍ ከበራሪ እንስሳ ወገን እንዳትባል አጥቢ ናት፤ ሙሉ በሙሉ ከአጥቢ እንስሳ ወገን እንዳትባልም ሌላው ተፈጥሮዋ ሁሉ እንደ በራሪ እንስሳ ነው። ብቻ የሁለት ዓለም ፍጡር! ዛሬም እንዲሁ በቁጥር ቀላል የማይባል የአማራ ልሂቅ ቀን ቀን "አማራ የተደቀነበት አደጋ የፈጽሞ መጥፋት አደጋ ነው" ሲል ይውል እና ሌሊት ላይ "አንድነት" የምትባለዋን የሌሊት ልብሱን ደርቦ ያውም ገና ፍትህ ያላገኘውና ዛሬም ወደ ራማ እየጮኸ ያለው የአማራ ህዝብ ደም በእጃቸው ላይ ካለ ሰዎች ጋር ፖለቲካዊ መዳራትን ይፈጽማል። ይባስ ብሎም ቀን ላይ የነገረህን ትቶ "ሁሉም ብሄር በወያኔ ተጨቁኗል፤ የአማራም ችግር ቢሆን በኢትዮጵያዊነት ማዕቀፍ ውስጥ ይፈታል" ይልሃል።

እንዲያው "እናቱ ገበያ የሄደችበትና፥ እናቱ የሞተችበት እኩል ያለቅሳል" ካልሆነ በስተቀር ከአማራ ውጪ የትኛው የኢትዮጵያ ብሔር ነው በሃያ ስድስት ዓመታት ብቻ ከሃያ ጊዜ በላይ በሙቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎቹ ያፈሩትን ንብረት እንኳ እንዳይሰበስቡ በመንፈግ የተፈናቀለው? ከአማራ ውጪ የትኛው ብሔር ነው ዘሩን እንዳይተካ በመድሃኒት የመከነው? ከአማራ ውጪ የትኛው ብሔር ነው በጅምላ የተጨፈጨፈው? ከአማራ ውጪ የትኛው ብሔር ነው ህፃን፣ ሴት፣ ሽማግሌ ሳይል በገደል ከነነብሱ የተወረወረው? ከአማራ ውጪ የትኛው ብሔር ነው 'የህዝብ ቁጥርህ በደዌ ተመናምኗል' ተብሎ እያለ እንደሌለ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቹ ያለበጀት በድህነት ሰንሰለት እንዲገረፉ የተደረገው? ከአማራ ውጪ የትኛው ብሔር ነው ቢ.ፒ.አር በሚል ሽፋን በጅምላ ከስራ ገበታው የተፈናቀለው? ከአማራ ውጪ የትኛው ብሔር ነው የመንግስት ሚዲያ በሚባሉት ሳይቀር የጥላቻ እና የስም ማጥፋት እንዲሁም የስነ ልቦና ጦርነት ሰለባ የሆነው? ከአማራ ውጪ የትኛው ብሔር ነው ከቦታ ቦታ እንዳይዘዋወር ባልተፃፈ ህግ የተከለከለው? ከአማራ ውጪ የትኛው ብሔር ነው ለም መሬቱን እየተነጠቀ ከአባቶቹ ምድር የተሳደደው? ብቻ በጣም ብዙ ነው።

አማራዊ ሆይ! የሌሊት ወፎቹ የሚነግሩህን "የአማራ ችግር በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ ይፈታል" የሚል ማደናገሪያ እና ማደንዘዣ ከንቱ ቅዠት ለመሆኑ እነዚህን በምድር ላይ ያሉ እውነቶች አስተውል።

ሲጀመር ነገሮች እንዲሁ በአርምሞ ከቀጠሉ ወያኔ እንደ ሀገር እየገነባት ያለውን ትግራይን በሁለት እግሯ ካቆማት በኋላ በተግባር የሞተችውን ኢትዮጵያ በአዋጅ መሞቷን ነግሮህ አንተን ምንም ባልተዘጋጀህበት በትኖህ ይሄዳል።

ሲቀጥል ሁኔታዎች ከቁጥጥሩ ውጪ እየወጡ ከሄዱ በአንድ ሌሊት ውስጥ ከሩቅ ይህን ቀን እየተጠባበቁ ያሉትን ኦነግንና ኦብነግን ሰብስቦ ሀገሪቱን እንደየድርሻቸው ተቃርጠዋት እብስ ሲሉ አንተ ምንም ባልተዘጋጀህበት አውላላ ሜዳ ላይ ቀሪ ነህ። በዚህም ሳያበቃ ለቀጣይ ጥቃትም የተመቻቸህ ትሆናለህ። ያለው ነባራዊ ሃቅም ሆነ ሊመጣ ያለው ነገር ይህ ከሆነ ዘንዳ በሁለት ሃሳብ የሚያነክሱት የሌሊት ወፎች የሚሏት ድህረ-ወያኔ ኢትዮጵያ የት ነው ያለችው? ወትሮውንም አይናቸውን አንድም ባለማወቅ አልያም በረብ ስላሳወሩት እንጂ አይደለም ነገ ዛሬስ ኢትዮጵያ መቼ ኖረችና?

አማራዊ ሆይ! ከዚህ በኋላ የአማራ ህዝብ ሰቆቃ የሚቆመው በውክልና ሳይሆን በአንተ በአማራዊው ተጋድሎ ብቻ ነው!!! ፍፁም ዕረፍት የምታገኘውም በቁዳር ድንኳኖች ሳይሆን አባት ሀገር ግዮናዊውን የአማራ ሀገር ስትመሰርት ብቻ ነው። ስለሆነም አንድ እጃቸውን በ"አንድነት" መንደር አድርገው በሌላ እጃቸው አማራዊ ወጪትህ ውስጥ ገብተን ካልፈተፈትን የሚሉትን አትፍቀድላቸው!!!

እንዲሁ ባለማወቅ በሁለት ሃሳብ የምታነክሱ የአማራ ልሂቃን የአጥንታችን ፍላጭ፥ የስጋችንም ቁራጭ እንደሆናችሁ ከማንም በላይ እናውቃለን። የእኛ ተቃውሞ እና ፀብ የህዝባችንን ሰቆቃ እንዲራዘም እያደረገ ካለው በሁለት ሃሳብ ከሚያነክሰው አስተሳሰባችሁ ጋር ብቻ ነው።

የሰው ልጅ ልክ እናንተ የደነቀራችሁብንን አይነት ተግዳሮት ሲገጥመው አይደለም የሰውን ልጅ የእግዚአብሔርን መልዓክ እንኳ "ከእኛ ወገን ነህ? ወይስ ከጠላቶቻችን?" ብሎ እንደሚጠይቅ ከእግዚአብሔር ነብይ ከኢያሱ አይተናል። እኛም እንጠይቃለን ወይ ከእኛ ጋር አልያም ከጠላቶቻችን ጋር ወግኑ።

**4ኛ. ስዬዎች /The Egocentric/**

የዛሬ ሰባት ዓመት አካባቢ ቀንደኛ ወያኔ የነበረው እና አሁንም የሆነው ስዬ አብርሃ ከእስር ሲፈታ የቆሰለ አውሬ ሆኖ ነበር። ራሱ በዋናነት የመሰረተውን ሥርዓት በግል ጋዜጦች ከማብጠልጠል ጀምሮ ፖለቲካ ፓርቲ እስከመመስረት ደረሰ። ይባስ ብሎም እስከ ዛሬ እንደዚህ እጅ እጅ የሚል መጽሐፍ አንብቤ የማላውቀውን "ፍትሕ እና ዳኝነት በኢትዮጵያ" የሚል መጽሐፍ ፃፈ፤ ኧረ ይባስ ብሎም የአሜሪካው ዲያስፖራ መድረክ አዘጋጅቶ ጋበዘው። ታድያ ይሄን ሁሉ "በተቃውሞ" ጎራ ከተጓዘ በኋላ በድንገት መለስ የመሞቱ ነገር ተሰማ። በቃ መለስ ሲሞት የስዬም ተቃዋሚነት አብሮ ሞተ እና ወደ ዘመዶቹ ተቀላቀለ። ወትሮውንም የግል ፀብ እንጂ የአመለካከት ልዩነት አልነበረውም። እንዲያው የግል ፀቡን የአመለካከት ልዩነት ያለ በማስመሰል ደጋፊን ከኋላ ለማሰለፍ የተደረገ ስልት ነበር።

ዛሬ ይሄንን መሰሪ ሰው ለምሳሌነት የተጠቀምኩት በቁጥር ብዙ ባይባሉም ሊያሳድሩ ከሚችሉት ተፅዕኖ አንፃር "እኔ፣የእኔ፣ለእኔ" በሚል ግለኛ አመለካከት ታጥረው በግል "አንድነት" ከምትባለው ጎራ ጋር ስለተጣሉ ብቻ የግል ተቃርኗቸውን የአማራነት ካባ ደርበውላት ተከታዮችን ለማፍራት እንደሚጥሩ ከአንዳንድ የአማራ ልሂቃን እያየን ነው። ነገ የግል ቁርሿቸው በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ሲያሽር ዛሬ አንቅረን ተፍተነዋል ያሉትን ነገ ተመልሰው እንደሚልሱት እርግጥ ነው። ስለሆነም አማራዊ የሆንክ ሁሉ ማንም ሄደም መጣም ያንተ ተጋድሎ ግለሰቦችን ማዕከል ያደረገ ሊሆን አይገባም። ያንተ ተጋድሎ ግዮናዊ አባት ሀገርህን እስክትመሰርት እና ነፃነትህን እስክታረጋግጥ እንጂ ግለኞች እስከሚወርዱበት የግማሽ መንገድ ፌርማታ ሊሆን አይገባም።

**የኃያላኑ ቀስት እንደምን ተሰበረ?**

/ክፍል ሶስት/

በክፍል አንድ እና ሁለት የአማራ ህዝብ ለባህርይውም ይሁን ለባህሉ እንዲሁም ለማንነቱ የማይስማማውን ጥቃትን ተሸክሞ የመኖርን ልማድ ሰብሮ እንዳይወጣ የገጠሙትን ውስጣዊ ተግዳሮቶች አይተናል። በክፍል ሶስት ውጫዊ ተግዳሮቶችን እንመለከታለን፥ መልካም ንባብ።

***መግቢያ፡-***

ነገራችንን ከቻይናው የጦር ጄነራል፣ ስትራቴጂስት እና ፈላስፋ ሰን ዙ በተዋስናቸው ሁለት አባባሎች እንዲህ እንጀምራለን።

1. "ጠላትህን እወቅ፤ ራስህንም እወቅ። ያኔ የመሸነፍ ስጋት ሳይገባህ መቶ ጦርነቶችን ማድረግ ትችላለህ።"
2. "ጦርነትን የማሸነፊያው ምርጡ መንገድ የጠላትን የጦርነት ስልት ማኮላሸት መቻል ነው።"

የአማራ ህዝብ በሶስት ሺህ ዓመት ታሪኩ እንደ ትግሬ - ወያኔ አይነት ጠላት ገጥሞት አያውቅም። ይህ የሆነበት ትልቁ ምክንያት ትግሬ - ወያኔ በአማራ ህዝብ ላይ፡-

- የተከተለው የጦርነት ስልት፣
- የጦርነት አይነት፣
- እንዲሁም በተግባር ካፈረሳት በኋላ ለኢኮኖሚ ጥቅሙ ሲል በቀጭን ድር ለጊዜው እንዳትፈርስ ባሰራት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከተለው አስተዳደራዊ ባህርይ እና
- ኢ-መደበኛ የወያኔ ሰራዊት የሆነው አጠቃላዩ የትግሬ ህዝብ ሚና ድምር ውጤት ነው።

ስለሆነም እነዚህን ነጥቦች በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን።

**1. ትግሬ - ወያኔ በአማራ ህዝብ ላይ የተከተለው የጦርነት አይነት፡-**

በመሠረቱ እንደ ወያኔ አይነቱ ህዳጣን /minority/ ቡድን በብዙሃን ላይ በተለይ እንደ አማራ ህዝብ ባለ የረጅም ጊዜ የጦርነት ልምድ እና የድል ታሪክ ባለው ህዝብ ላይ ጦርነትን አውጆ ጊዜያዊም ቢሆን ድል መጨበጥ የሚችለው መብረቃዊ ምት /Blietz-Krieg/ በሆነ የጦርነት አይነት ሳይሆን የተኛው አንበሳ እንዳይነቃ በመጠንቀቅ ቀስ በቀስ እየገዘገዘ በመጣል / Frog-Boiling Tactic/ ነው።

ይህ በእንግሊዝኛ ቋንቋ "ፍሮግ ቦይሊንግ" የሚባለው የጦርነት አይነት ስያሜውን ያገኘው በባዮሎጂ ላብራቶሪ ውስጥ የተደረገ ሙከራን ተከትሎ ነው። እንቁራሪት በተፈጥሮዋ የመዝለል ችሎታ አላት። እናም የፈላ ውሃ ውስጥ ብትጥላት ወዲያው ተፈናጥራ ትወጣለች። ነገር ግን በመጀመሪያ ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ አድርገሃት ውሃውን በጣም ቀስ እያልክ ሙቀቱን ብትጨምረው ምቾት እየተሰማት በመጨረሻም ተፈናጥራ መውጣት በማትችልበት ደረጃ እየተዳከመች ትመጣ እና ተቀቅላ ትሞታለች።

አማራዊ ሆይ! ያቅለሸልሸንም፥ ይዋጥልንም ሃቁ ግን ወያኔ ከአርባ አመት በፊት በግልፅ እና በህቡዕ በእኛ ላይ ያወጀውና እንደ ካንሠር እየገዘገዘ አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ ያደረሰን የጦርነት አይነት ይኸው "ፍሮግ ቦይሊንግ ታክቲክ" ነው።

ታዲያ አንተ አማራዊ! ለአርባ አመታት ሙቀቱ እየጨመረ የመጣውን መከራ የሌለ ያህል ረስተህ የሚያስብ አዕምሮ እንደሌላት እንቁራሪት ጊዜያዊ ምቾትህን እያሰብክ እስከመጨረሻው ተቀቅለህ መጥፋትን? ወይስ እንደ አያቶችህ፣ እንደ ወግህ እና እንደ ልማድህ እግርህን ለጠጠር፥ ደረትህን ለጦር በመስጠት ከመከራው ባህር ተፈናጥረህ መውጣት ነው ያለብህ?

ዛሬ ወያኔ የራስ ደጀን ተራራን መለስኩ ቢልህ፣ የጭን ገረዱ ብአዴን የአማራን ክልል በኢንደስትሪ ሊያጥለቀልቅ ትልቅ የቢዝነስ ዕቅድ አወጣ ቢልህ፣ በምኒልክ አደባባይ ላይ ወጣት ካድሬዎቹን ሰብስቦ አድዋን ለመዘከር "ተኩሶ መሳት፥ ዘርቶ አለማጨድ አላውቅም እኔ፤ እምቢ…" እያስባለ ቢያስፎክር፣ ስቴዲየም ገነባልሃለሁ ቢልህ፣ " ትግሬና አማራ ወንድማማች ነው የወልቃይትም ጉዳይ በሰላም ይፈታል" ቢልህ የመከራውን ሙቀት መጨመር እንዳታስተውል በኋላም ከረፈደ በኋላ ልክ እንደ እንቁራሪቷ ከተዘፈቅበት መከራ መውጣት ተስኖህ ተቀቅለህ እንድትጠፋ ማደንዘዣ ነውና አትስማው!!!

**2. የትግሬ - ወያኔ በአማራ ህዝብ ላይ የተከተለው የጦርነት ስልት፡-**

ቱርኮች በአርመኖች ላይ፣ ናዚዎች በአይሁዶች ላይ እንዲሁም ሰርቦች በቦስኒያውያን ላይ የተከተሉት የጦርነት ስልትም ይሁን የፈፀሙት የዘር ፍጅት ፍፁም የሆነ የሃይል የበላይነታቸውን መሰረት ያደረገ እና መደበኛ በሚባለው መንገድ በመሆኑ ያደረሱት የጥፋት ልክ በቀላሉ መታየት የሚችል ነው።

ነገር ግን ትግሬ ወያኔ እንደ ቱርኮች፣ ናዚዎች እና ሰርቦች እኩይ የዘር ፍጅት ወንጀሉን በመደበኛው መንገድ ልፈፅም ቢል የአማራ ህዝብ በቀላሉ ሊነሳበት እና እንዳያገግም አድርጎ እንደሚጨፈልቀው ስለሚያውቅ የተከተለው ስልት ኢ-መደበኛ /Unconventional or Dirty Warfare/ የሆነ የጦርነት ስልትን ነው። ለግንዛቤ ይረዳን ዘንድ ዋና ዋናዎቹን በዝርዝር እንደሚከተለው እናያለን።

**ሀ. ሌበንስ ራውም/Living Space/፡-**

አዶልፍ ሂትለር እና ፓርቲው ናዚ ወደ ስልጣን ሲመጡ እንመሰርተዋለን ብለው ያሰቡትን ለሺህ ዓመት ለሚዘልቀው ስርወ መንግስት መሠረት ይሆናል ብለው የተነሱበት አንዱ ጉዳይ "ለምርጦቹ" የኤርያን ዝርያዎች የመኖሪያ ስፍራ ወይም በጀርመን ቋንቋ "ሌበንስ ራውም" ማዘጋጀት ነው። ስለሆነም እጅግ ለም የሆነው እና ለእርሻ ተስማሚ የሆነው የዩክሬን እና የሩሜንያ

መሬት፣ በነዳጅ እና በተፈጥሮ ጋዝ የበለፀገው የአዘርባይጃን ምድር እና የካስፒያን ባህር፣ የራሽያ ወርቅ እና ሰፊ ግዛት እንዲሁም ለጉልበት ስራ የሚፈለጉት የማዕከላዊ ኤዥያ ሀገራት ዜጎች የናዚ ወረራ ኢላማ ሆኑ።

በተመሳሳይ የትግሬ ወያኔ ቡድን በአማራ ህዝብ ኪሳራ እና ፈፅሞ መጥፋት ላይ "ታላቋን" ትግራይ "ወርቅ" ለሆኑት ትግሬዎች ይገነባ ዘንድ ቃፍታ ሁመራን፣ ወልቃይትን፣ ጠገዴን፣ ጠለምትን፣ ኮረምን፣ እንዳ መሆኒን፣ አላማጣን፣ራያ አዘቦን እና ሌሎችንም ከአማራ ታሪካዊ ይዞታ በመውሰድ እና በራሱ ሀገር በማጠቃለል እንዲሁም ትግሬን በማስፈር እና አማራዊውን በረቀቀ መንገድ እንዲጠፋ አልያም እንዲሰደድ አድርጓል። በዚህም ሳይወሰን አማራን ከሱዳን ጋር ወሰን እንዳይኖረው በማድረድ በተቃራኒው ትግራይን ከቤኒሻንጉል እና ጋምቤላ ጋር የሚያገኛኝ ካርታ ሰርቷል።

አማራዊ ሆይ! ስለዚህ ካርታ ስነግርህ ወያኔ በራሱ የቴሌቪዥን ጣቢያ ሴፕቴምበር 16 2016 ዓ.ም. ቀርቦ "እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2002 በታተመው የ10ኛ ክፍል የስነ-ዜጋ መፅሃፍ ላይ በገፅ 24 የታተመው የክልሎችን ይዞታ የሚያሳየው ካርታ ስህተት ስለሆነ………..." ብሎ "ይቅርታ" የጠየቀበትን መፅሃፍ ዋቢ አድርጌ ከመሰለህ ተሳስተሃል።

ሩቅ መሄድ ሳያስፈልግ ጆን ያንግ የተባለው የወያኔ ቅጥረኛ ጋዜጠኛ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1989 ዓ.ም. Peasant revolution in Ethiopia፡ The Tigray People's Liberation Front, 1975-1991 በሚል ባሳተመው መጽሃፉ ላይ ኢትዮጵያ ከሚገኘው UNDP አገኘሁት የሚለውን ካርታ እንደ ግብዓት ተጠቅሞበታል። እኔም ከዛው መጽሀፍ ላይ ያለውን ምስል ከዚህ ጽሁፍ ጋር አያይዤዋለሁ። በእርግጠኛነት UNDP የሀገሪቱን ካርታ የሚያገኘው ከወያኔው የካርታ ስራዎች ድርጅት ነው። ታዲያ "ቢያዩኝ እስቅ፥ ባያዩኝ እሰርቅ" ካልሆነ በቀር ከመጀመሪያው ጀምሮ በተለይ በሀገሪቱ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ የውጭ ድርጅቶች የተሰጣቸው ካርታ ወያኔ የውጪውን አለም እያለማመደበት ሲሆን በተጠና መልኩም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለመማሪያነት በመጠቀም ትውልዱን በዚህ መልክ ሊቀርፀው የሄደበት መንገድ እንጅ በስህተት የተደረገ አልያም አሁን የተዘጋ አጀንዳ አይደለም።

የወያኔም የመጨረሻ ግብ ይህን ካርታ እውን ማድረግ እና ከወሰዳቸው መሬቶች በተጨማሪ በዚህ ካርታ ላይ እንደሚታየው ትግሬን ከቤኒሻንጉል እና ጋምቤላ ጋር የሚያዋስን ቀጭን ኮሪደር በመፍጠር በኢንደስትሪ፣ በማዕድን እና በለም መሬት የበለፀገ "ሌበንስ ራውም" ለቀጣዩ የትግሬ ትውልድ መፍጠር ነው። እንዲሁ ለጠቅላላ ዕውቀት ይረዳ ዘንድ ወያኔ በጋምቤላ የትግሬ ባለሃብቶችን ብቻ ሳይሆን መንዳካ ደሃ የሆነውን ትግሬ ሳይቀር እንዴት እያሰፈረ እና ጋምቤላዎችን በረቀቀ መንገድ ሀገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ እና ዳግም እንዳይመለሱ እያደረገ ያለውን ማወቅ የሚፈልግ ሰው ፍሬድ ፒርስ The Land Grabbers በሚል ከፃፈው መጽሐፍ ላይ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ማንበብ በቂው ነው።

ለአማራዊው ግን እንዲህ እንላለን፡- እሴትህ ከሆነው ሥነ-ቃልህ መካከል የቀደሙት አባቶችህ እንዲህ ይሉ ነበር "አማራ በርስቱ፥ አምላክ በመንግስቱ ሲመጡበት አይታገስም'።" እውነት ነው መለኮታዊውን ዙፋን ይጋርድ ዘንድ የተፈጠረው ኪሩብ፣ የውበት ሁሉ መደምደምያ ሆኖ የተፈጠረው ኪሩብ በአምላክ መንግስት ላይ ሲነሳ ምህረት የለሽ ቅጣት ተቀጥቷል። እውነት ነው የቀደሙ አማራውያን ርስታቸውን ግዮናዊውን ሀገራቸውን ለመውረርም ሆነ ለመንጠቅ የመጣን ኃይል እንደ ነብር ተቆጥተው እንደ አንበሳም በክንዳቸው አድቅቀው ጠላትን ወደ መጣበት እንደ ሸርት ውሃ እንዲፈስ አድርገዋል። ታዲያ የዛሬው ትውልድ አማራዊ ሆይ! ይህ ሁሉ ርስት ሲወሰድብን ከቶ እንደምን ዝም እንላለን? ይኸው ዝም ስላልን እኮ ነው ትግሬን በተፈጥሮ ሀብት እና በለም መሬት ለማደላደል ሲባል ሌላ ቀጭን ኮሪደር መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ሌላው ርስታችንም ሊወሰድ የታሰበው።

አማራዊ ሆይ! አንተ የተዳፈንክ እሳት ሆነህ በላይህ ላይ ሊረማመድ ያለውን የምትፋጅ ረመጥ እንጂ የእሳት ልጅ አመድ የምትባልማ አይደለህም።

አይደለም በርስታችን ላይ ቀጭን የመሸጋገሪያ ኮሪደርን መስራት፤ የተወሰዱብንን ይዞታችንን ሳናስመልስ፣ በግፍ እንዲጠፉ የተደረጉ የወገኖቻችንን ደም ሳንመልስ፣ ለዘለቄታው አባት ሀገራችንን ግዮናዊውን የአማራን ሀገር ሳንመሠርት እረፍት የለንም፤

ሊኖረንም ከቶ አይገባም!!! ለዚህ ደግሞ ያንተም፣ የእኔም፣ ያንቺም፣ የእሱም፣ የእርሷም፣ የሁላችንም የአማራውያን ሃላፊነት እና ግዴታ ነው!!!

## ለ. ማጠልሸት፣ ማሰይጠን እና ስያሜ መስጠት /Defamation, Demonization and Name Calling/

ከናዚ ሽንፈት ማግስት በኋላ በጀርመኗ ኑረንበርግ ከተማ የተሰየመው የጦር ወንጀለኞች ፍርድ ቤት ለፍርድ አቅርቦ በስቅላት እንዲቀጡ ካደረጋቸው ወንጀለኞች መካከል ዩሊዩስ ሽትራይከር አንዱ ነበር። ሽትራይከር የፖለቲካ መሪ አልያም ወታደራዊ አዛዥ አልነበረም። ሽትራይከር መርዝ የሚተፋ ብዕር ባለቤት የሆነ ጋዜጠኛ ነበር። ይህ ሰው ለዘመናት አብረው በኖሩት አይሁዶች እና ጀርመኖች መካከል ትልቅ ገደል እንዲፈጠር ትልቅ ሚና የተጫወተው የአይሁዶችን ገፅታ እና ታሪክ በማጠልሸት እና ማንነታቸውን በማሰይጠን የአንዱ መኖር ለሌላው አለመኖር እንደሆነ በተባ መርዘኛ ብዕሩ ሳያሰልስ በመፃፉ በሂደት እጅግ ስልጡን የሚባለው የጀርመን ማህበረሰብ የዚህ ሰው ፕሮፓጋንዳ ሰለባ መሆን ቻለ። እናም የሆነው ሁሉ ሆነ።

አማራዊ ሆይ! ወያኔ ትግሬ ገና ከጥንስሱ አፉን የፈታው ያንተን አማራዊ ገጽታህንና ታሪክህን በማጠልሸት እንዲሁም ማንነትህን በማሰይጠን እና ነውረኛ ስሞችን እየለጠፈብህ እንደሆነ ከ68ቱ የራሱ ማኒፌስቶ ባሻገር የወያኔ ትግሬ መስራች የነበረው አረጋዊ በርሄ ለዶክትሬት መመረቂያ ካዘጋጀው A political history of the Tigray People’s Liberation Front (1975-1991): Revolt, ideology and mobilization in Ethiopia በተሰኘው መጽሐፉ ገጽ 201 ላይ ቃል በቃል እንዲህ ይላል፡- " anti-Amhara propaganda was subtly encouraged within the movement. Cultural events, theatrical performances as well as jokes and derogatory remarks were used to disseminate this poisonous attitude.. በግርድፉ ሲተረጎምም "ፀረ-አማራ ፕሮፓጋንዳ በህወሃት ውስጥ በረቀቀ መንገድ ይበረታታ ነበር። ባህላዊ ዝግጅቶች፣ድራማና ቴአትር እንዲሁም ቀልዶችና አማራን የሚያንቋሽሹ አስተያየቶች ይህን መርዘኛ /ፀረ-አማራ/ አስተሳሰብ ለማስፋፋት ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር።"

ያኔ ገና ሲፀነስ በጥቂት የወያኔ ሽትራይከሮች የተጀመረው ይህ የስነ-ልቦና ጦርነት ወያኔ ትግሬ ማዕከላዊውን መንግስት ሲቆጣጠር የመንግስትን ሚዲያ ሳይቀር እየተጠቀመ የጦርነቱን አድማስና ጥልቀት በማስፋት አማራዊ የሆነ ሁሉ በየሄደበት እንዲሳደድ እንደ ርኩስም እንዲታይ ተደረገ። በሀገሪቱ የሚገኙ ከአማራ ውጪ የሆኑ ሁሉ እየተከፈላቸው ፀረ-አማራ ትምህርት በሴሚናር እንዲወስዱ ተደረገ፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ክረምት ክረምት እየተከፈላቸው ይህ አመለካከት እንዲሰርጽባቸው ብዙ ተሰራበት። በውጤቱም እነዚህ የተሻለ ግንዛቤ አላቸው የሚባሉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሀገር ሰላም ብለው በማደሪያቸው የተኙ አማራዊ ተማሪዎችን በስለት አንገታቸውን አረዱ። ይህ ደግሞ እኔ የዚህ ጽሑፍ ፀሃፊ በአካል ያየሁት እንጂ በሩቅ በስማ በለው የሰማሁት አልያም ያነበብኩት አይደለም። ይባስ ብሎም እንደ ጅን ያንግ ያሉ ቅጥረኞችን በመጠቀም በውጪው ዓለም ሳይቀር የአማራን ገጽታ ማጠልሸት እና ተክለ ስብዕናውን ማሰይጠን ቻለ። የተከፈላቸው እነ ፖል ሄንዝም በየጋዜጣው ላይ በአማራዊው ላይ የሚችሉትን ያህል ወረዱበት። ይህም አማራዊው በውስጥም በውጭም እንዲነጠል እና ያለከልካይ የጥቃት ሰለባ እንዲሆን አደረገው።

በክፍል ሁለት ላይ በስፋት የዳሰስናቸው የአማራ ልሂቃንም ምንም ማምጣት እንደማይችሉ የተረዳው ትግሬ ወያኔ ቀድሞ "የቡርቃ ዝምታ" በሚለው ልብ ወለድ መጽሐፍ ላይ ያሰፈረውን በአካል ሀውልት አድርጎ "የአማራ የሰይጣንነት ምልክት" ይሆን ዘንድ አኖሌ ላይ አቆመው። ይህ የስነ-ልቦና ጦርነትም እጅ እና እግር እያወጣ ሲሄድ በሌላ መድረክ "አንቱ" ያልናቸው የኛው ሰዎች አራጆቻችን በተሰበሰቡበት መድረክ እየተገኙ ሊመሰገኑ የሚገባቸውን ጀግኖች አማራዊ ቀደምቶቻችንን ያለሃጥያታቸው እየወነጀሉ "በነሱ ጥፋት እኛ ልንወቀስ አይገባም" የምትል መርዘኛ ሀረግ አምጥተው መነፋረቁን ስራዬ ብለው ተያያዙት። ስህተት ሲደጋገምም ትክክል እየመሰለ በመሄዱም የእኛው ሰዎች የጠላት የስነ-ልቦና ጦርነት ሰለባ እንደሆኑ በአንድ ምሳሌ እንይ። ይሁኔ በላይ የሚባለው የባህል ዘፋኝ "ሰከን በል" የሚል ዘፈን መልቀቁ የሚታወስ ነው። በዘፈኑ ኦፊሻል ቪዲዮ ላይ በ4ኛው ደቂቃ ከ7ኛው እስከ 14ኛው ሰከንድ ባለው ጊዜ ውስጥ ያለው ግጥም እንዲህ ይላል፡-

" አንዱ አንዱን ሳይገድለው ደምም ሳይፋሰስ
በወላጁ ጥፋት ልጁ ሳይወቀስ
ተባብሮ ተፋቅሮ.................. " እያለ ይቀጥላል።

እኔ ለማሳየት የፈለኩት ለምሳሌ አንድ ሰው አባትህ ነብሰ ገዳይ ነው ቢልህ ከማንም በላይ አባትህን በቅርብ የምታውቀው አንተ ለዛ ሰው የምትሰጠው ምላሽ መሆን ያለበት "አይ አንተ ውሽታም እና የእኔም የአባቴም ጠላት ነህ " ነው? ወይስ "በአባቴ ጥፋት እኔ ልወቀስ አይገባም" ነው ማለት ያለብህ? አንድ ሰው በማሰቢያው ላይ አካላዊ ጉዳት ከሌለበት አልያም የስነ ልቦና ችግር ሰለባ ካልሆነ በቀር ሁለተኛውን ለምርጫም እንዲቀርብ መፍቀድ የለበትም።

አማራዊ ሆይ! ጠላትን መለማመጥ መፍትሄ የሚያመጣ ቢሆን ኖሮ የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ቼምበርልን ሂትለርን እየተለማመጠ የያኔዋ ቼኮዝሎቬኪያ ይዞታ የነበረውን የዙደተንላንድ ግዛት በእጅ መንሻነት ሂትለር እንዲወስድ ቢስማማም ሂትለርን የልብ ልብ ሰጠው እንጂ አላስቆመውም።

አይሁዶች አንተ አማራዊው ዛሬ የገጠመህን አይነት ተግዳሮት ሲገጥማቸው ያደረጉት ነገር በብዙው ረድቷቸዋል። ለሚሰነዘርባቸው የስም ማጥፋት፣ገጽታን የማጠልሸት እና ታሪካቸውን የማሰይጠን ተግባር እግር በእግር እየተከተሉ እነሱም ምላሽ መስጠት በመቻላቸው ይኸው ዛሬም ከፍ ብለው ይኖራሉ። ለዚህ ደግሞ Anti-Defamation League እና AIPAC የሚባሉት የሎቢ ድርጅቶቻቸው ተሞክሮ ለእኛ አማራውያንም ጥሩ ትምህርት ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ለምሳሌ በ2013/2014 አካባቢ ፍልስጤማውያን ከሌሎች አረቦች ጋር በመሆን BDS /Boycott, Divestment and Sanction/ የሚል የአይሁዶችን የኢኮኖሚ አቅም ለማሽመድመድ ዘመቻ በሚዲያ ሲጀምሩ አይሁዶቹም በቅርጽ ተመሳሳይ በትርጉም ግን የሚለይ BDS /Bigotry, Dishonesty and Shame/ የሚል ዘመቻ በመክፈት እና የሞራል ልዕልና በመያዝ የተከፈተባቸውን የስነ-ልቦና እና የኢኮኖሚ ጦርነት መመከት ችለዋል። ከዚህም ብዙ ልንማር የምንችለው እንዳለ ይሰማኛል።

አማራዊ ሆይ! እስኪ ንገረኝ በምን ስሌት ነው የገዳዩ እና አረመኔው ዮሐንስ ልጅ የምኒልክን ልጅ ገዳይ የሚል? ጎጃም እና ወሎን በደም አባላ ያጠበው ትግሬው ዮሐንስ አይደለም እንዴ? ምኒልክ የማረከውን ንጉስ የሚሾም፣ የማረካቸውን ወራሪዎች አሳክሞ ወደ ሀገራቸው የሚልክ ሆኖ ሳለ ትግሬው ዮሐንስ አይደል እንዴ የማረከውን ንጉስ አይኑን አስጠፍቶ በግፍ የገደለ? አማራዊውን ንጉስ ቴዎድሮስን እንዲሞት ምክንያት የሆነው ማነው? ትግሬው ዮሐንስ አይደለም እንዴ መንገድ እየመራ ያመጣቸው? የወሎ አማሮችን በሃይማኖት ሽፋን የጨፈጨፈው ትግሬው ዮሐንስ አይደለም እንዴ? ለመሆኑ ከመቼ ጀምሮ ነው ክርስትና በሰይፍ መስፋፋት የጀመረችው?ክርስትና ሰይፍ ሲመዘዝባት እንጂ ሰይፍ መዝዛ አታውቅም።በስሟ የመዘዙትም ከራሳቸው ምድራዊ ፍላጎት የዘለለ ምንም ሃይማኖታዊ መሰረት አልነበራቸውም ሊኖራቸውም አይችልም።ዮሐንስም በአማራ ላይ ባለው ጥላቻ ምክንያት ሃይማኖትን እንደሽፋን ተጠቀመበት እንጂ ሃይማኖተኛ ቢሆንማ ኖሮ የማረከውን ንጉስ አይኑን በማጥፋት አያሰቃየውም ነበር።

አማራዊው ወገናችን ሆይ! ጠላታችንን እና የተከፈተብንን የጦርነት ስልት ካወቅን ልክ እንደ አይሁዶቹ ለዛ ምላሽ መስጠት የሁላችንም ታሪካዊ አደራ እና የዚህ ትውልድ ፈተና ነው። ዛሬ ላይ ከስነ-ልቦና ጦርነት እስከ መሳሪያ አንስተን ለመፋለም ካልቆረጥን ነገ ፈፅሞ የእኛ ቀን አይደለችም። ዛሬ በጉብዝናችን ወራት ያልሰራናት ያቺ ነገ ነገ ላይ የእኛ ቀን እንድትሆንም መጠበቅ የለብንም።




**የኃያላኑ ቀስት እንደምን ተሰበረ?**

/ክፍል አራት/

ለማስታወስ ይረዳ ዘንድ በክፍል አንድ እና ሁለት የአማራ ህዝብ ለባህርይውም ይሁን ለባህሉ እንዲሁም ለማንነቱ የማይስማማውን ጥቃትን ተሸክሞ የመኖርን ልማድ ሰብሮ እንዳይወጣ የገጠሙትን ውስጣዊ ተግዳሮቶች አይተናል። እንዲሁም በክፍል ሶስት ውጫዊ ተግዳሮቶችን ማየት እንደጀመርን የሚታወስ ነው። በዚህም የአማራ ህዝብ በሶስት ሺህ ዘመን ታሪኩ እንደ ትግሬ - ወያኔ አይነት ጠላት ገጥሞት እንደማያውቅ፤ ይህ የሆነበትም ትልቁ ምክንያት ትግሬ - ወያኔ በአማራ ህዝብ ላይ የተከተለው የጦርነት አይነት፣ የጦርነት ስልት፣ እንዲሁም በተግባር ካፈረሳት በኋላ ለኢኮኖሚ ጥቅሙ ሲል በቀጭን ድር ለጊዜው እንዳትፈርስ ባሰራት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከተለው አስተዳደራዊ ባህርይ እና ኢ-መደበኛ የወያኔ ሰራዊት የሆነው አጠቃላዩ የትግሬ ህዝብ ሚና ድምር ውጤት መሆኑን ከዘረዘርን በኋላ ወያኔ ትግሬ በአማራ ህዝብ ላይ እየተከተለ ካለው

የጦርነት ስልት ውስጥ ሁለቱን በዝርዝር በማየት በይደር ማቆማችን ይታወሳል። እነሆ ዛሬ ክፍል አራትን እንዲህ ጀመርን፤ መልካም ንባብ።

**ለግንዛቤ**

በዚህ ክፍል ውስጥ እንደ ምሳሌ መነሳት ያለባቸው ዓለም አቀፍ ክስተቶች በመኖራቸው የጀርመን እና የፈረንሳይ ስያሜ እና ቃላት ተጠቅመናል። ስለሆነም እንደየሀገራቱ የቋንቋ አጠቃቀም ስለሚነበቡ አንባቢው ሲያነብ የአፃፃፍ ግድፈት ሳይሆን ቃላቶቹ እና ስያሜዎቹ በነዚህ ሀገራት ቋንቋ በተፃፉት መልክ እንደሚነበቡ ከወዲሁ ያስተውል።

**ሐ. ታሪክን መጠምዘዝ እና በቁጥሮች መጫወት /Re-writing History and Data Massaging/፡-**

**መ. ውክልና መንፈግ /Denial of Representation/:-**

አንድን ህዝብ ውክልና መንፈግ የጊዜ ጉዳይ እንደሆን እንጂ ብዙ ዋጋ እንደሚያስከፍል ታሪክ ህያው ምስክር ነው። የናዚ ፓርቲን ወደ ስልጣን ያመጣውና ሁለተኛው የአለም ጦርነት እንዲነሳ ምክንያት የሆነውም ይኸው ነው። "ታሪክን አሸናፊዎች ይጽፉታል" ሆኖ እንጂ ጀርመኖች ለናዚ ልባቸውን የከፈቱት እንደሚባለው የሂትለር አንደበተ ርቱዕነት አማሏቸው፣ የጎብልስ ፕሮፓጋንዳ ማርኳቸው፣ የሮዘንበርግ መሬት-አርድ ንድፈ-ሃሳብ አሸንፏቸው፣ የኸርማን ጎሪንግ የማደራጀት ብቃት መስጧቸው አልያም ሃይንሪሽ ሂምለር እንደ ሰም አቅልጦ እንደ ገል ቀጥቅጦ እጃቸውን ስለጠመዘዛቸው አልነበረም።

ጀርመን በማርች 14- 1918 ዓ.ም. አንደኛውን የአለም ጦርነት እያሸነፈች እና በድል ዋዜማ በነበረችበት በጥቂት ወራት ልዩነት ድንገት የነበረው ሁሉ እንዳልነበር ሆኖ በኖቬምበር 1918 እጅ ሰጠች፤ ሲቀጥልም ለ 14 ዓመታት የዘለቀው መከራቸው አንድ ብሎ ጀመረ።

ጀርመኖቹ በኖቬምበር 1918 የደረሰባቸውን አሰቃቂ ሽንፈት በቋንቋቸው እንዲህ ይገልፁታል "Dolchstoß' /ዶልሽ ስቶስ/ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ /Stab-in the-back/ ሲባል በአማርኛ ተመጣጣኝ ትርጉም ብንፈልግለት "በጭቃ ውስጥ እሾህ መወጋት" አልያም "በሳር ውስጥ እባብ መነደፍ" ሊባል ይችላል።

ለማንኛውም የሆነው እንዲህ ነው። የጀርመንን የንግድና የሠራተኛ ማህበራትን የተቆጣጠሩት በወረቀት እንጂ በደም ጀርመናዊ ያልሆኑት አይሁዶች በኑዮርክ እና ለንደን ከነበሩ የትላልቅ የፋይናንስ እና የባንክ ተቋማት ባለቤቶች ጋር በመመሳጠርና ሳቦታጅ በመፈጸም እንዲሁም የስራ ማቆም አድማ እያስደረጉ ለጦሩ የሎጅስቲክ አቅርቦት እንዲስተጓጎል ከማድረግ ጎን ለጎን ሚዲያውን የተቆጣጠሩት ተመሳሳይ ሰዎች የጦሩን እና የህዝቡን ሞራል በመስበር ትልቅ ሚና ተጫወቱ። አብዮት በማስነሳትም በኖቬምበር 11፥ 1918 ዓ.ም. የፖለቲካ ስልጣኑን በመያዝ ጀርመን ጦርነቱን መሸነፏን ተቀበሉ። እነዚህ በደም ጀርመናዊ ያልሆኑ ነገር ግን የጀርመንን ህዝብ እንወክላለን ያሉት ሰዎች በጀርመን ማህበረሰብ ዘንድ "Novemberverbrecher" /ኖቬምበር ፌርብሬሽር/ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ "The November Criminals" ወይም በአማርኛ "የህዳር ወንጀለኞች" በመባል ይታወቃሉ ። እነዚህ የህዳር ወንጀለኞች በጁን 1919 ዓመተ ምህረት በፈረንሳይዋ የቬርሳይ /Versailles/ ከተማ በመገኘትም "ከአሸናፊዎቹ" /እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ እና አሜሪካ/ ጋር የቬርሳይ ስምምነትን /The Treaty of Versailles/ ፈረሙ። በመሰረቱ የቬርሳይ ስምምነት 440 አንቀፆች የነበሩት ሲሆን 414ቱ ጀርመንን በመቅጣት ላይ የሚያጠነጥኑ ነበር።

ወገንህ ያልሆነ ሰው እወክልሃለሁ ሲል ከአለት የጠጠረውን ሸክም እንድትሸከም ከጠላትህ ጋር በላይህ ላይ እንዴት እንደሚደራደር የቬርሳይ ስምምነት አንዱ ማሳያ ነው።

ይህን ሁሉ ማንሳታችን በይዘት ተመሳሳይ የሆነ ወንጀል ወያኔ ትግሬ እና በደም ትግሬ በሆኑ የዚህ ዘመን "የህዳር ወንጀለኞች" ስብስብ የሆነው ብአዴን የሚባለው ቡድን አማራዊውን በሁለት መልክ ውክልና በመንፈግ የፈፀሙትንና እኛ አማራውያን

መቼም ቢሆን ይቅር ልንል የማንችለውን ወንጀል እንዴት እንደፈፀሙብን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መልኩ ለማሳየት ይረዳን ዘንድ ነው።

**መ.1. የሽፍጥ ውክልና /Fraudulent Representation/፡-**

እንደሚታወቀው ወያኔ ትግሬ ማዕከላዊውን መንግስት ከተቆጣጠረ በኋላ ሀገሪቱን በዘውግ ፌደራሊዝም /Ethnic Federalism/ እንድትተዳደር ሲያደርግ በሀገሪቱ የሚገኙ ብሄሮች በሙሉ ይወከለናል የሚሉትን ድርጅት ሲመሰርቱ እና እንዲመሰርቱ ሲደረግ አማራዊው ግን ይህ እድል ተነፍጎት ይልቁንም ከ17 ዓመት በፊት "በኢትዮጵያ ውስጥ የአማራ የበላይነት አለ፤ አማራ እንደብሔር ጨቋኝ ነው" ብሎ በአማራዊው ላይ ከከተማ እስከ ገጠር ጦር ያወጀበት ሃይል የትናንቱ ኢህዴን የዛሬው ብአዴን በደም የራሱ ያልሆነን እና በጠላትነት የፈረጀውን ህዝብ እንዲወክል ተደረገ። ይህ የአማራነትን ጭምብል ለብሶ በዋናነት በትግሬ የሚዘወረው ብአዴን የሚባለው ቡድን ተመሰረትኩ የሚለው ህዳር 11 ሲሆን ከጀርመኑ "The November Criminals" /"የህዳር ወንጀለኞች"/ ጋር የስምም የግብርም ተመሳሳይነት ያለው ቡድን ነው።

ኤርትራዊው በረከት ስምዖን፣ ትግሬው ህላዊ ዮሴፍ፣ ትግሬው ታደሰ ካሳ /ጥንቅሹ/፣ ትግሬው ዮሴፍ ረታ /ገይድ/፣ ትግሬው ካሳ ተክለ ብርሃን፣ የትግሬ ዲቃላው አለምነው መኮንን፣ ኦሮሞው ደመቀ መኮንን፣ ደቡቡ ተፈራ ዋልዋ፣ የትግሬ ዲቃላው ዮሴፍ አንተነህ፣ የትግሬ ዲቃላው ወንደሰን ታደሰ፣ በእናቱ ወገን የትግሬ ዲቃላ የሆነው አዲሱ ለገሠ /ቆቱ/፣ የኦሮሞ ዲቃላዋ ገነት ዘውዴ እና መሰሎቻቸው በበላይነት የሚዘውሩት ብአዴን ገና ከጅምሩ አማራዊውን ይወክላል ማለት በጎችህን ተኩላ እንዲጠብቅልህ አደራ የማለት ያህል ነበር።

ስለሆነም የጀርመንን ጭምብል አጥልቀው ኑዮርክ እና ለንደን ከነበሩት ወገኖቻቸው ጋር ሸፍጥ እንደሰሩት የኖቬምበር ወንጀለኞች ሁሉ የአማራነትን ጭንብል ያጠለቁ ትግሬዎች ከወገናቸው ወያኔ ጋር በመሆን ላለፉት 26 ዓመታት አማራዊው ፖለቲካዊ ውክልና እንዳይኖረው፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ እንዳይከበርለት ይልቁንም በተጠና እና በረቀቀ መልኩ ህልውናው እንዲከስም ዛሬም ተግተው እየሰሩ ይገኛል። በዚህም ሳይወሰን "የአማራ ክልል" ብሎ ወያኔ ትግሬ ሸራርፎ በከለለው ክልል ውስጥ የደህንነት እና የፖሊስ ሀይሉን በበላይነት የሚያስተዳድሩት ትግሬዎች ሲሆኑ እንዲሁም ቁልፍ በሆኑ የኢኮኖሚ እና ሲቪል ተቋማት ውስጥ ከላይኛው እስከ መካከለኛው የስልጣን እርከን እና ተዋረድ እንዲሁ በትግሬ ተወላጆች የተያዘ ነው። ቀዳሚ ተግባራቸውም፡-

- ኢኮኖሚያዊ የስለላ ተግባር /Economic Espionage/ መፈፀም፤

- የክልሉ የተፈጥሮ ሀብት በትግሬ ተወላጆች እጅ እንዲሆን ማድረግ /Wealth Transfering/

ምሳሌ፡- በባህር ዳር የትላልቅ ሆቴል እና ሰፋፊ መሬት ይዞታ ባለቤቶች እነማን እንደሆኑ ማወቁ ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው። እንዲሁም በጎንደር ከተማ ውስጥ እንደ አንበጣ በቢዝነሱ ላይ የመስፈራቸው እንቆቅልሽ ፍቺ የዚሁ አካል ነው።

- የክልሉን ልማት ማደናቀፍ /Bureaucratic Sabotage Tactic/

ምሳሌ፡- "በአማራ ክልል" ይገነባሉ ተብሎ የመሰረት ድንጋይ ከተቀመጠ በኋላ እንዲኮላሽ የተደረጉ በርካታ ኢንደስትሪዎች አይነተኛ ማሳያ ናቸው።

- "ለአማራ ክልል" ተብሎ የሚሰጡ የእርዳታ ገንዘብን ስራ ላይ እንዳይውል በማድረግ ገንዘቡን ወደ ትግራይ እንዲዛወር ማድረግ /Budget Deflection Tactic/

- ኤፈርት በመባል የሚታወቀው የወያኔ የንግድ ኢምፓየር ለሚያመርታቸውም ሆነ ከውጭ ለሚያስመጣቸው ሸቀጦች "በአማራ ክልል" ገበያን መፍጠር እና ማመቻቸት /Opportunity Maker-Opportunity Taker Approach/ ምሳሌ፡- 1. "በአማራ ክልል" ውስጥ የሚሰሩ የገጠር መንገዶች በሙሉ በኤፈርቱ የሱር ኮንስትራክሽን የተሰሩና እየተሰሩ ያሉ ናቸው።

ምሳሌ፡- 2. "በአማራ ክልል" ውስጥ በየመንደሩ የሚገነቡ ኮሌጅ እና ዩኒቨርሲቲ ተብዬ የድንጋይ ክምሮች ሲሚንቶ አቅራቢ የትግሬው መሰቦ እንደሆነ ይኸው ከሰሞኑ አይናቸውን በጨው ታጥበው ነግረውናል። ሲቀጥልም ይሰራሉ ለተባሉት ዘጠኝ ስቴዲየሞችም ሲሚንቶ አቅራቢው ይኸው የትግሬ መሰቦ ፋብሪካ ነው። ታዲያ ከዚህ በላይ ገበያን መፍጠር እና ማመቻቸት ምን አለ?

- "በአማራ ክልል" የሚገኙ ጥንታዊ ቅርሶችን በረቀቀ እና በተጠና መልኩ ማዘረፍ እና ማሸሽ /Removing-the Fire-from-Under- the -Cooking-Pot Tactic/

የዚህ ተግባራቸው ዋነኛ ዓላማ የህዝቡን ታሪካዊ አሻራ ማጥፋት፣አዲሱ አማራዊ ትውልድ በወያኔ የሚፃፈውን የሀሰት ታሪክ በተጨባጭ በማስረጃ እንዳይሞግት ለማድረግ እንዲሁም አዲሱ አማራዊ ትውልድ የአባቶቹ የታሪክ አሻራ የሌለው ወፍ ዘራሽ ሆኖ እንዲታይ ለማድረግ ብሎም በሂደት የክልሉን የቱሪዝም ገቢ እያዳከሙ ለማጥፋት የሚፈፀም ወንጀል ነው።

- "በአማራ ክልል" በሚገኙ ተቋማት ውስጥ /ለምሳሌ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፣ የባህርዳሩ ፈለገ ህይወት ሆስፒታል....../ ውስጥ በቦርድ አባልነት በመግባት ተቋማቱን ማዳከም /The Inner Front Tactic (Destroying from within)/

- "በአማራ ክልል" የሚመረቱ የግብርና ምርቶችን የትግሬ ነጋዴዎች በጅምላ ሂሳብ በርካሽ ዋጋ ከተመረቱበት ቦታ እንዲገዙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና የትግሬን የምግብ አቅርቦት ዋስትናን ማረጋገጥ። ለዚህም ነው ላለፉት ሰባት ተከታታይ አመታት ሀገሪቱ በተለይ ኦሮሚያ እና የሶማሌ ክልል በረሃብ ሲጠቁ ለወትሮው ረሃብ እና ጠኔ ዘመዱ የሆነው የትግሬ ህዝብ ጠግቦ የሚያድረው።

ከዚህ ጎን ለጎን ወያኔ ትግሬ እና የአማራነትን ጭምብል የለበሰው የትግሬ ቡድን የእኔ የሚለው ወኪል የሌለውን አማራዊውን ከታሪካዊ ይዞታው በማፈናቀል፣ ትግሬ ከኤርትራ ጋር በተጣላ አማራዊው ወጣት በገፍ ለፈንጂ አምካኝነት እንዲመለመል በማድረግ፣ ህዝባችን ኑሮው እንዲቆረቆዝ፣ ህልውናውም እየከሰመ እንዲመጣ በአጠቃላይም ህዝባችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እፎይታ እንዳያገኝ ልክ በሁለት የቴኒስ ተጫዋቾች መካከል ወዲህ እና ወዲያ እንደምትላጋ የቴኒስ ኳስ እረፍት አልባ አድርገውታል። ይህን በታሪካችን ሆኖ የማያውቀውን የአናሳዎች ሴራ መበጣጠስ፣ ወደ ቀደመ ክብራችን መመለስ፣ አባት ሀገራችንን ግዮናዊውን የአማራን ሀገር መመስረት በዚህ አማራዊ ትውልድ አዕምሮ እና ክንድ ላይ የወደቀ የወገን አደራ ነው!!!

## መ.2. የብዙኃን ውክልና መብትን መንፈግ /Denial of Representation for the Majority in a Multi-Ethnic Society/

ወያኔ ትግሬ ማዕከላዊ መንግስቱን ሲቆጣጠር ሀገሪቱን በዘውግ ፌደራሊዝም /Ethnic Federalism/ እንዳዋቀራት ግልፅ ነው። ይህ የፌደራል ሥርዓት በባህርይው ዝንፍ /Asymetric/ እንደሆነ የሚያሳብቁ በርካታ ነገሮችን መዘርዘር ቢቻልም ከላይ ለተነሳንበት ሃሳብ ማሳያ ይሆን ዘንድ አንዱን ብቻ በመምዘዝ ወያኔ ትግሬ በአማራዊው ላይ እያደረሰበት ያለውን ጥፋት እናያለን።

እንደሚታወቀው ራሳቸውን ሐረሪ ወይም አደሬ እያሉ የሚጠሩ ህዳጣን /Minority/ ህዝቦች በሀገሪቱ ካለው ነባራዊ ሁኔታም ሆነ ታሪካዊ አመጣጥ አንፃር በቁጥርም ይሁን በአሰፋፈራቸው እዚህ ግባ ሊባሉ የማይችሉ፤ በዛ ቢባል በልዩ ዞን ሊተዳደሩ

ሲገባ ሌሎች በቁጥርም ይሁን በታሪካዊ አሰፋፈራቸው ከነሱ የተሻሉ ህዝቦች ያላገኙትን የራሳቸውን ክልል በችሮታ መልክ "የሐረሪ ሕዝቦች ክልል" በሚል ተሰጣቸው።

ይህ "የሐረሪ ሕዝቦች ክልል" በተለምዶ "የአማራ ክልል" ከሚባለው ክልል ውጪ ከአዲስ አበባ ቀጥሎ በምጣኔ /ratio/ የአማራውያን ቁጥር ከፍ ብሎ የሚገኝበት ክልል ሲሆን ክልሉን በሚያስተዳድረው የሀረሪ ክልል ምክር ቤት ውስጥ በዋናነት አደሬዎች ሲገኙ የኦሮሞዎች ቁጥር ከአማራውያን ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ በመሆኑ በምክር ቤቱ ውስጥ ውክልና አላቸው። ይሁን እንጂ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ዛሬም ድረስ የአማራውያን ተወካይ በሀረሪ ምክር ቤት ውስጥ እንዳይገባ በግልጽ የተከለከለ ሲሆን በዚህ እና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የያኔው " የህዳር ወንጀለኞቹ" /ብአዴን/ አውራ፥ የዛሬው ፓስተር ነኝ ባይ ታምራት ላይኔ "እነሱ /የሀረር አማራውያንን/ ነፍጠኞች ናቸው" ብሎ መሳለቁ መቼም የሚዘነጋ አይደለም። እርግጥ ነው የትግሬ ዲቃላው አለምነው መኮንንም በቅርቡ ተመሳሳይ ነገር መናገሩ ይታወሳል።

በመሆኑም በሀረር /"በሐረሪ ሕዝቦች ክልል"/ የሚኖሩ ወኪል አልባ አማራውያን ላይ የሚከተሉት ዘግናኝ ግፎች ተፈጽመውባቸዋል፥ እየተፈፀሙባቸውም ነው:-

- በከፍተኛ ሁኔታ አማራውያንን ከክልሉ ነቅሎ የማጥፋት ስራ /Intensive De-Amharization Programme/ በመሰራቱ በ1994 ዓ.ም. በክልሉ ይኖሩ የነበሩ አማራውያን ቁጥር 32.6% የነበረ ሲሆን በ2007 ዓ.ም. በተደረገው ቆጠራ በክልሉ የሚኖሩ አማራውያን ቁጥር በአስደንጋጭ ሁኔታ ወደ 22.77% አሽቆልቁሏል። አስገራሚው ነገር በክልሉ የሚገኙ የሌላ ብሄር ተወላጆች ቁጥር በ1994 ከነበረው ቁጥር አንጻር ጭማሪ ሲያሳይ በአማራውያን ላይ የተፈፀመውን የረቀቀ የዘር ማጽዳት ዘመቻ ተከትሎ የአማራውያን ቁጥር ከላይ በተገለጸው መልኩ ቀንሷል።

- በተለምዶ የሀረር የገበያ ማዕከል እየተባለ በሚጠራው ስፍራ የሚገኙ የአማራውያን የንግድ ተቋማት ሆን ተብሎ በተደጋጋሚ በእሳት እንዲወድም በመደረጉ አማራውያን በተጠና መልኩ እንዲደኸዩ /Impoverished by Design/ እንዲሁም ከኖሩበት እና ሀብት ካፈሩበት ስፍራ እንዲነቀሉ ዳግምም እንዳይመለሱ ተደርጓል።

- በሀረር ተወልደው ያደጉ አማራውያን በክልሉ /"በሐረሪ ሕዝቦች ክልል"/ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ተቀጥረው እንዳይሰሩ /Denial of Access and Opportunity/ ባልተፃፈ ህግ ተከልክለዋል።

- ለወትሮው የአማራውያን ይዞታ የነበሩ መሬቶች "ለልማት" በሚል ሰበብ ያለምንም ካሳ እና ተለዋጭ መሬት በግፍ እንዲነጠቁ /Forcible Expulsion/ ተደርጎ ለአደሬዎች ተሰጥቷል።

- በሀረር /"በሐረሪ ሕዝቦች ክልል"/ የሚገኙ አማራውያን የህግ ከለላ ማግኘት አይችሉም። በተለይ ወንጀል ፈፃሚው አደሬ ከሆነ እና ወንጀል የተፈፀመበት አማራዊ ከሆነ የተገላቢጦሽ ተበዳዩን አማራዊ በመወንጀል /Blaming the Victim Tactic/ፖሊስም ሆነ ፍርድ ቤት ወንጀሉን ከመመርመርና ከማጣራት ይልቅ አማራዊውን በቀጥታ ወደ እስር ቤት በመወርወር አልያም ወደ ክልሉ ተመልሶ እንዳይገባ በማስፈረም ያባርሩታል። ይህ አይነቱ አሰራር በሀረሪ ክልል በአማራውያን ላይ በተደጋጋሚ የሚፈፀም ሲሆን የተባረረው ሰው ተወልዶ ካደገበት ስፍራ እንዲነቀል እና ዳግም እንዳይመጣ የሚያደርጉበት አንዱ ስልት ነው።

**ሰ. ጥላቻን ማስረፅ /Aversion Therapy/**

በመሰረቱ በግላጭም ይሁን በረቀቀ ዘዴ የሚፈፀም የዘር ማጥፋት ወንጀል በጊዜ ውስጥ ራሱን እያጎለበተ የሚመጣ ሂደት እንጂ ድንገተኛ ክስተት አይደለም። የሂደቱ መጀመሪያ ደግሞ ወንጀሉን የሚፈፅመው ቡድን ወንጀሉ የሚፈፀምበትን ማህበረሰብ መደበቂያ እንዲያጣ፣ የተገለለ እና የተጠላ እንዲሆን ማድረግ ነው። በመሆኑም ወያኔ ትግሬ የራሱ መሰረት በሆነው የትግሬ

ህዝብ ዘንድ እንዲሁም በሌሎች የሀገሪቱ ብሔሮች ዘንድ አማራዊው የተጠላ እና የተገለለ እንዲሁም ለቀጣይ ጥቃት ያለከልካይ የተጋለጠ እንዲሆን ጥላቻን ያሰረፀበትን መንገድ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

**ሰ.1. ወያኔ ትግሬ ፀረ-አማራ ጥላቻን በትግሬ ማህበረሰብ ውስጥ ለማስረፅ የተጠቀመባቸው ስልቶች**

1.ማሳበብ /Scapegoating Tactic/:- እንደሚታወቀው ወያኔ ትግሬ ወደ በረሃ በወረደ ማግስት ማኒፌስቶ-68 የተሰኘ የድርጅቱን መርህ የሚያሳይ ሰነድ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የተከሰቱ አለማቀፋዊ እና አካባቢያዊ ለውጦችን ተከትሎ መጠነኛ የቅርጽ እና የመጠን ጥገናዊ ማሻሻያ ከማድረግ ባሻገር ዛሬም ድረስ የወያኔ ትግሬ አስኳል መርህ ከዚህ ሰነድ እንደሚቀዳ የአደባባይ ምስጢር ነው። በመሆኑም በዚህ ሰነድ የተለያዩ ክፍሎች ላይ እንደተገለፀው በትግሬ ህዝብ ላይ ደረሰ ለሚሉት ችግር ሁሉ መንስዔው የአማራ ህዝብ እንደሆነ ከሰነዱ ላይ የተወሰኑትን ብቻ ወስደን ማየት በቂ ነው።

ምሳሌ 1. "ራስን መጣል (ዲ-ሁማናይዜሽን)" በሚለው ርዕስ ስር እንዲህ ይላል፡-

"ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ የሚሄደው የኢኮኖሚ ብዝበዛ በሰፊው የትግራይ ህዝብ ላይ ድሕነት፣ ረኃብና ውርደት እየተደጋገመ እንዲደርስ አድርጓል። በተጨማሪም የትግራይ ህዝብ ለረጅም ዘመን ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቱ ተነፍጎ ሲጠላና ሲናቅ እንዲሁም አድልዎ ሲፈጸምበት ቆይቷል። ይህም በደል ጨቋኝዋ የአማራ ብሔር ሆነ ብላ እንደመንግሥት መመሪያዋ አድርጋ ስትሰራበት የቆየች ሲሆን ፋሽስታዊ ደርግም በባሰና በመረረ መንገድ ቀጥሎበታል። ከዚህም የተነሳ ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ኑሮው እንዲቆረቁዝ ተደርጓል። በዚህ ምክንያት የሥራ ማጣት ችግር፣ ሽርሙጥናና ስደትን ከማስከተሉም በላይ ራስን መጣልና መንከራተት የትግራይ ሕዝብ ዕለታዊ ተግባሩ ሆኖ ይገኛል። ስለሆነም ሕዝቡ ተጠርጣሪና የተጠላ እንዲሆን በመደረጉ በህብረት መኖር የማይችል ሆኖ ይገኛል።"

ምሳሌ 2. "የህበረተሰቡ ወደ ኋላ መቅረትና ዕረፍት ማጣት" በሚለው ርዕስ ስር እንዲህ ይላል ፡-

"ሰፊው የትግራይ ህዝብ ሥራ አጥቶ በሽሙጥናና በስደት ወ.ዘ.ተ. ብቻ ሳይሆን በረኃብ፣ በድንቁርናና በበሽታ እየተሰቃየ ይኖራል። እነዚህም ችግሮች ወንጀል እንዲፈጽም ይገፋፉታል።

ለችግሩ መሠረታዊ ምክንያት ኢምፐርያሊዝምና ባላባታዊ ሥራዓቱ ይሁኑ እንጅ ጨቋኛዋ የአማራ ብሄር የምታደርገው የኢኮኖሚ ብዝበዛና የፖለቲካ ጭቆና ታክሎበት ነው። ከዚህም በላይ የሚያኮራው የህዝባችን ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ እንዲደከምና ተዳክሞ እንዲጠፋ ወይም የአማራ ብሔር የገዥ መደብ ጥቅም እንዲጠበቅ የ፫ ሺ ዓመታት ታሪክና ባህላችን መመኪያቸውና መፎከሪያቸው ሆኖ ይገኛል። ይህ የታሪክ ስርቆት በአንድ በኩል ደግሞ ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ታሪክ እንደሌለው ሕዝብ እንዲያስቆጥረው የተደረገ የመንግሥት መመሪያ ነው። ቢሆንም የትግራይ ህዝብ ቁጮንና ተቃውሞውን በቁጣና በጥላቻ በብዙ መንገድ ደጋግሞ ገልጾዋል። ይህና ይህንን የመሳሰሉ አድሃሪ ድርጊቶች አሁንም ያለው ፋሽስታዊ መንግሥትም ስለቀጠለበት ሰብዓዊ ክብሩና መብቱ እስኪመለስለት ድረስ ሰፊው የትግራ ህዝብ ትግሉን አያቋርጥም። ጨቋኝዋ የአማራ ብሔርም ጭቆናዋ እስካላቆመች ድረስ ህብረተሰባዊ እረፍት አታገኝም።"

በሌላ በኩል እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በሜይ 1983 በሁለተኛው ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ ይፋ የተደረገው የወያኔ ትግሬ ድርጅታዊ ፕሮግራም /PEOPLE'S DEMOCRATIC PROGRAMME OF THE TIGRAY PEOPLE'S LIBERATION FRONT (TPLF): Adopted by the Second Organizational Congress of the TPLF May 1983/ ላይ የትግሬን ችግር በሙሉ በአማራ ህዝብ የተፈጠረ ለማስመሰል ብዙ ርቀት እንደተጓዘ ማየት ይቻላል።

በአጠቃላይ ወያኔ ትግሬ ለአገዛዙ መሰረት በሆነው የትግሬ ህዝብ ውስጥ አማራን እና አማራዊነትን በጠላትነት ለማስረፅ ባለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት ማኒፌስቶ ቀርጾ፥ ድርጅታዊ ፕሮግራም ነድፎ ቀን ከሌት ሳይታክት በመስራቱ ዛሬ እያንዳንዱ ትግሬ የአማራን ህዝብ ከሀሞት በመረረ ጥላቻ ሊያየው ችሏል።

**2. ታሪክን ማጣመም /Re-writing History/፡-**

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው ወያኔ ትግሬ በማኒፌስቶው እና በድርጅታዊ ፕሮግራሙ ታሪክን ለራሱ ዓላማ በሚመች መልኩ እያጣመመ የትግሬን የችግር ምንጭ የአማራ ህዝብ እንደሆነ አስመስሎ ከማቅረቡ ባሻገር እንደ ብስራት አማረ እና "መምህር" ገብረ ኪዳን ደስታ የሚባሉ ነፍሰ ገዳይ ትግሬዎችን "ታሪክ ፀሐፊ" የሚል ካባ በማስለበስ ታሪክን እያጣመሙ የአማራን ህዝብ እንዲጠላ የሚያደርጉ መጽሐፎችን በትግሬኛ እና በአማርኛ ቋንቋ አሳትመው በተለያዩ ጊዜ ያሰራጩ ሲሆን ለአብነት ያህልም የብስራት አማረ "ፍኖተ ገድል" የተሰኘው አንዱ ነው። የወያኔ ትግሬ የስለላ ሰራተኛ እና ቀደም ባሉት ጊዜያት የእስር ቤት ገራፊ የነበረው ብስራት አማረ ይህንን መጽሐፍ አዲስ አበባ በተለምዶ 22 እየተባለ በሚጠራው አካባቢ በሚገኘው አክሱም ሆቴል ያስመረቀ ሲሆን ስብሃት ነጋ፣ አባይ ፀሐዬ እና ስዩም መስፍንን ጨምሮ በርካታ የወያኔ ሰዎች የተገኙ ሲሆን ዝግጅቱን በሙዚቃ ያጀቡት ከስዊድን የተጋበዘው አበበ አርአያ /እምበር ተጋዳላይ/ እና ትርሃስ ታረቀ ነበሩ። አማራዊ ሆይ! ትግሬ ካላጠፋህ ላይተኛ ተማምሏል የምንልህ ትግሬ ላንተ መጥፋት ከአሜሪካ እና ከአውሮፓ ሳይቀር እየተጠራራ ሲያሴር በአይናችን እንዲህ በማየታችን ነው!!!

በሌላ በኩል "መምህር" ገብረኪዳን ደስታ የተባለው ወያኔ ትግሬ ካሳተማቸው ፀረ-አማራ መፃህፍት መካከል በአማርኛ ቋንቋ የታተመው "የትግራይ ህዝብና የትምክህተኞች ሴራ ከትናንት እስከ ዛሬ" የሚለው ሲሆን በትግሬኛ ቋንቋ የታተመው "እምቢታ አንፃር ወረርቲ (ታሪኽ ዘመነ መዋእል ሃፀይ ዮሃንስ 4ይ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ)" የሚለው ነው። በነገራችን ላይ የዚህ መጽሐፍ ምረቃ ዝግጅት የተካሄደውም ሆነ ወጪው የተሸፈነው በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ነው። ከዚህ ባሻገር ይህ መጽሐፍ ዛሬ በትግራይ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደማጣቀሻ መጽሐፍ እንዲወሰድ በትግራይ የትምህርት ቢሮ አማካኝነት ተደርጓል።

**3. መደበኛ ትምህርት ቤቶችን መጠቀም /Systemic Brainwash Tactic/፡-**

የናዚ ፓርቲ ፀረ-አይሁድ መርሆውን ሰፊ መሠረት ለማስያዝ ይረዳው ዘንድ ከተጠቀመበት መንገድ በዋነኝነት የሚጠቀሰው "ተተኪ ትውልድን በፓርቲ መርህ መቅረጽ" የሚለው በጥላቻ የተሞላ ስልት ሲሆን ይህን ተግባራዊ ለማድረግ መደበኛ ትምህርት ቤቶችን እና የትምህርት ስርዓቱን በመጠቀም በራስ አምሳል ተተኪን ማፍራት መቻል ነው። በተመሳሳይ ዛሬ በትግራይ የትምህርት ቢሮ እውቅና እና በጀት የሚታተሙ እና በየትምህርት ቤቱ የሚገኙ የታሪክ መጽሐፎች፣ማጣቀሻ መፃህፍት እንዲሁም በምንባብ መልክ በቋንቋ መጻህፍት ላይ የሰፈሩ ጽሑፎች ተተኪ የትግሬ ትውልዶች ስር የሰደደ የአማራ ህዝብ ጥላቻ ይዘው እንዲያድጉ አድርጓቸዋል፤ አሁንም እያደረጋቸው ይገኛል። በዚህ አጋጣሚ በዚህ ጉዳይ በእጃችን የሚገኙ ማስረጃዎችን ሙሉ በሙሉ የትርጉም ስራውን ስንጨርስ በበቂ ሁኔታ አጠናክረን ለአማራዊው ወገናችን ይፋ እንደምናደርግ ከወዲሁ ለማሳወቅ እንወዳለን።

**4. ሙዚቃን እና አጠቃላይ ጥበብን መጠቀም /Absorbing High Culture Tactic/፡-**

የዚህ ጽሑፍ አንድ አካል በሆነው ክፍል 3 ላይ ለማሳየት እንደሞከርነው የወያኔ ትግሬ መስራች የነበረው አረጋዊ በርሄ ለዶክትሬት መመረቂያ ካዘጋጀው A political history of the Tigray People's Liberation Front (1975-1991): Revolt, ideology and mobilization in Ethiopia በተሰኘው መጽሐፉ ገጽ 201 ላይ ቃል በቃል እንዲህ ይላል፡- " anti-Amhara propaganda was subtly encouraged within the movement. Cultural events, theatrical performances as well as jokes and derogatory remarks were used to disseminate this poisonous attitude.. በግርድፉ ሲተረጎምም "ፀረ-አማራ ፕሮፓጋንዳ በህወሃት ውስጥ በረቀቀ መንገድ ይበረታታ ነበር። ባህላዊ ዝግጅቶች፣ድራማና ቴአትር እንዲሁም ቀልዶችና አማራን የሚያንቋሽሹ አስተያየቶች ይህን መርዘኛ /ፀረ-አማራ/ አስተሳሰብ ለማስፋፋት ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር።" ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ትናንት በረሃ ሆነው ያደረጉት ሳይበቃ ዛሬ የተተካው አዲሱ የትግሬ ሙዚቀኞች ትውልድ የአማራን ህዝብ የሚያንቋሽሹ እና ጥላቻን የሚዘምሩ ዘፈኖቻቸውን ከሀገር ውስጥ አልፈው በአውሮፓ እና ሰሜን አሜሪካ መድረኮች ላይ ማቀንቀናቸው የተለመደ ተግባር ሆኗል። በዚህ አጋጣሚ በዚህ ጉዳይም እንዲሁ

ያሰባሰብናቸውን ነባር እና አዳዲስ ፀረ-አማራ ጥላቻን የሚሰብኩ የትግሬ ዘፈኖችን በቅርብ ለአማራዊው ከነትርጉማቸው ይፋ እንደምናደርግ ቃል እንገባለን።

**5. ሬድዮና የህትመት ውጤቶች /Controlling Mass Media/፡-**

በዚህ ረገድ የወያኔ ትግሬው "ወይን " የሚለውን መጽሔት ስራዬ ብሎ ለተከታተለ ሰው የናዚው ሳምንታዊ "ዴር ሽቱርመር " የተሰኘውን ጋዜጣ እንዲያስታውስ ያደርገዋል፤ እንዲሁ "ድምጸ ወያነ" የተሰኘው ሬድዮን ስታዳምጥ የሩዋንዳው RTLM የተሰኘው የጥላቻ የሬድዮ ጣቢያ ትዝ ይልሃል። በነገራችን ላይ አዲሱ ለገሠ የተባለው የህዳር ወንጀለኞች ቁንጮ ከጥቂት ወራት በፊት በነዚህ ሚዲያዎች የአማራ ተጋድሎን አስመልክቶ ቃለ ምልልስ ያደረገ ሲሆን የአማራን ህዝብ በመከፋፈል እና አማራዊውን ቅማንት ከወንድሙ የአማራ ህዝብ እየነጠለ " አማራዎች በጎንደር ይኖሩ በነበሩ ትግራዋዮች ላይ ከመነሳታቸው በፊት በቅማንት ህዝብ ላይ ተነስተው ጭፍጨፋ ፈጽመዋል " እያለ " እወክለዋለሁ" የሚለውን ህዝብ እንዴት እንደወከለው በተግባር አሳይቶናል። ከዚህ ጎን ለጎን እነዚህ ሚዲያዎች ከበረሃ እስከ አሁን ድረስ የሚተፉት ፀረ-አማራ ጥላቻ ለደቂቃ ያልተቋረጠ መሆኑን አማራዊው ልብ ሊለው የሚገባ እና ጠላቶቹ የት ድረስ ርቀው እንደተጓዙ ልብ ሊለው ይገባል።

**6. ፊልም፣ ሲኒማ እና ዘጋቢ ፊልሞች /Controlling the Social Sphere Tactic/:-**

በዚህ በኩል የትግራይ የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም የትግራይ ቴሌቪዥን በየጊዜው እያዘጋጁ የሚለቋቸው ዘጋቢ ፊልሞችን ለተመለከተ ሰው ትግሬም ሆነ ወያኔ ትግሬ በአማራ ህዝብ ላይ ያላቸው መራር ጥላቻ ምን ያህል ስር የሰደደ እንደሆነ እና እጃችንን አጣጥፈን ካየናቸው ሳያጠፉን እረፍት እንደሌላቸው መገንዘብ ይችላል።

አማራዊው ወገናችን ሆይ! መጪው ጊዜ ለእኛ ለአማራውያን እጅግ ፈታኝ እና አስቸጋሪ ነው። ይህንን አስጨናቂ ወቅት መሻገር የምንችለው፥ እንደህዝብም ህልውናችንን አስጠብቀን መኖር የምንችለው አንድ ነገር ካደረግን ብቻ ነው። በአማራዊነት ስንሰባሰብ እና የራሳችን የሆነውን አባት ሀገራችንን ግዮናዊውን የአማራ ሀገር ስንመሰርት ብቻ ነው። አለበለዚያ ከሩቅ እንደ ሰብዓ ባቢሎን፥ ከቅርብም እንደፍልስጤም የተበተንን ህዝቦች፤ በሰይፍም እንደጠፉት የሻርከ አይላንድ ህዝቦች አልያም በምድራቸው መፃተኛ እንደሆኑት እንደ አበርጅኖች መሆናችን አይቀርም። ይህ ክፉ ዕድል እንዳይገጥመን ምርጫው ዛሬ በእጃችን ነው። በአማራዊነት ዙሪያ መሰባሰብ፤ አባት ሀገራችንንም ለመመስረት ወደ ተግባር መግባት!!!

**ሰ.2. ወያኔ ትግሬ ፀረ-አማራ ጥላቻን በሌሎች የሀገሪቱ ብሔሮች ውስጥ ለማስረፅ የተጠቀመባቸው ስልቶች /Kill-with A-Borrowed-Knife Tactic (War by Proxy)/፡-**




**የኃያላኑ ቀስት እንደምን ተሰበረ?**

/ክፍል አምስት/

ለማስታወስ ይረዳ ዘንድ በክፍል አንድ እና ሁለት የአማራ ህዝብ እየደረሰበት ያለበትን ጥቃት ሰብሮ እንዳይወጣ የተጋረጡበትን ውስጣዊ ተግዳሮቶች አይተናል። እንዲሁም በክፍል ሶስት እና በክፍል አራት ውጫዊ ተግዳሮቶችን ማየት እንደጀመርን የሚታወስ ነው። በዚህም የአማራ ህዝብ በታሪኩ እንደ ትግሬ - ወያኔ አይነት ጠላት ገጥሞት እንደማያውቅ፤ ይህ የሆነበትም ትልቁ ምክንያት ወያኔ ትግሬ በአማራ ህዝብ ላይ የተከተለው የጦርነት አይነት፣ የጦርነት ስልት፣ እንዲሁም በተግባር ካፈረሳት በኋላ ለኢኮኖሚ ጥቅሙ ሲል በቀጭን ድር ለጊዜው እንዳትፈርስ ባሰራት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከተለው አስተዳደራዊ ባህርይ እና የወያኔ አገዛዝ ጠንካራ መሠረት የሆነው አጠቃላዩ የትግሬ ህዝብ ሚና ድምር ውጤት መሆኑን ከዘረዘርን በኋላ ወያኔ ትግሬ በአማራ ህዝብ ላይ እየተከተለ ካለው የጦርነት ስልት ውስጥ አራቱን በዝርዝር አይተን አምስተኛውን /ጥላቻን ማስረፅ (Aversion Therapy)/ በክፊል እንዳየን በይደር ማቆማችን ይታወሳል። እነሆ ዛሬ ክፍል አምስትን በዚህ መልኩ ጀመርን። መልካም ንባብ!!!

**ሠ.2. ወያኔ ትግሬ እና ግብረ አበሮቹ ፀረ-አማራ ጥላቻን በሌሎች የሀገሪቱ ብሔሮች ውስጥ ለማስረፅ የተጠቀሙባቸው ስልቶች /Kill-with A-Borrowed-Knife (War by Proxy Tactic)/፡-**

ይህ ፋሽስታዊ የትግሬ ቡድን ቢችል በተራዘመ የጊዜ ገደብ ውስጥ የአማራን ህዝብ ፈፅሞ ማጥፋት፥ አልያም ህዝባችን ዳግም ሊያንሰራራ በማይችልበት ሁኔታ አከርካሪውን ለመስበር ካለው ጥልቅ ፍላጎት አንፃር መሠረቱ በሆነው የትግሬ ህዝብ ውስጥ መራራ ጥላቻን እንዳሠረፀ ሁሉ በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ በሀገሪቱ በሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ አማራዊው የተጠላ እና ከሀገሪቱ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ምህዳር የተገለለ እንዲሆን የሚችለውን ሁሉ አድርጓል፤ እያደረገም ነው።

በዋናነትም ሁለት ዓይነት ጉልህ ሚናዎችን /Roles/ በመጫወት እና በእያንዳንዱ ሚናው ውስጥም ከግብረ አበር ተላላኪዎቹ ጋር የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም አማራዊው ፖለቲካዊም ይሁን ማህበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊም ይሁን ሥነ-ልቦናዊ ዕረፍት እንዳያገኝ ይልቁን በዚያች ሀገር ላይ ፍፁም የተጠላ እና የተገለለ እንዲሁም ለቀጣይ አስፈሪ ጥፋት ክፉኛ የተጋለጠ እንዲሆን አድርጓል።

በመሆኑም ፋሽስታዊው ወያኔ ትግሬ አማራዊው በሌሎች ዘንድ የተጠላ ይሆን ዘንድ በዋናነት የሚጫወተው ሚና የሚከተለውን ይመስላል፡-

ሀ. ኦህዴድ እና መሰል አሻንጉሊቶቹን በመገፋፋት እና በማበረታታት ፀረ-አማራ ጥላቻን በተለያየ ስልት በህዝባቸው እንዲያሰርፁ ማድረግ /Enabler's Role/

ለ. የቀጥታ ተሳትፎ በማድረግ እና በሌሎች ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ጥላቻን ለህዝቦቻቸው እንዲያስተምሩ በማድረግ /Direct Impact Role/

ስለሆነም በእያንዳንዱ የወያኔ ትግሬ ሚና ውስጥ የተጠቀመባቸውን አብይ የጥላቻ ስልቶችን እንደሚከተለው እናያቸዋለን።

**ሠ.2.1. በመገፋፋት እና በማበረታታት /Enabler's Role/፡-**

በዚህ የወያኔ ሚና ስር በዋናነት ወያኔ ትግሬ ከትልቁ ምስል ጀርባ ሲሆን በፊት ለፊት የሚታዩት አንድም እንደ አሻንጉሊት ጠፍጥፎ የሰራቸው እና ዛሬም ድረስ የሚጠቀምባቸው ኦህዴድ እና የሀረሪ ብሔራዊ ሊግን የመሳሰሉ ድርጅቶች /Delegets/ አልያም የነዚህ ድርጅቶች ሰለባ ሆነው ያደጉ "የቁቤው ትውልድ" እፍታዎች አልያም በአንድ ወቅት የወያኔ ትግሬ እና የሻዕቢያ ግርፍ የነበሩ የኦነግ ርዝራዦች ናቸው።

በመሆኑም ከትልቁ ምስል ጀርባ ያለውን ወያኔ ትግሬን ሳንረሳ እነዚህ ኃይሎች በአማራዊው ላይ የጥላቻ ዘመቻ የከፈቱበትን ስልት እና መንገድ እንደሚከተለው እንመለከታለን። ይህም አማራዊው ያለበትን አስደንጋጭ ሁኔታ ቆም ብሎ እንዲፈትሽ እና ከከበበው አስፈሪ አደጋ ራሱን ለዘለቄታው ይታደግ ዘንድ ቁርጠኛ አቋም እንዲይዝ እንዲሁም በአማራዊነቱ ተደራጅቶ ስለህልውናው መጠበቅ እና ስለ መፃኢ አባት ሀገሩ እውን መሆን በጽናት ይታገል ዘንድ ግንዛቤውን ያሳድግለታል ከሚል እምነት ነው።

**ሠ.2.1.1. ሐውልቶችን እና ገላጭ ምስሎችን ማቆም /Symbolic Imagery/፡-**

የቅርብ ጊዜ ታሪክ እንደሚያሳየው አንድ ማህበረሰብ ሌላኛውን ለማጥፋት በሚነሳ ወቅት ከሚያደርጋቸው ቅድመ ዝግጅቶች መካከል ተጠቂውን ማህበረሰብ በቃላት አልያም ገላጭ በሆኑ ምስሎች እና ሐውልቶች ከሰውነት ተራ ማውጣት /De-humanize/ ሲሆን ይህም ተጠቂው ማህበረሰብ በሂደት ለሚመጣበት ዕልቂት ሰብዓዊ ርህራሄ የማይገባው ይልቁን የመጣበት አደጋ ሁሉ በራሱ ድርጊት እና ባህርይ ምክንያት የመጣበት እንደሆነ ለማስመሰል እና ተጠቂውን ማህበረሰብ ተጠያቂ ለማድረግ ነው /"They Bring their own Misfortune" Approach/

ለምሳሌ የናዚ ፓርቲ አይሁዶችን ታህተ-ሰብዕ /"Untermensch" (Sub-human)/ እያለ ከመጥራት ጀምሮ አይሁዶች ህፃናትን አርደው ደማቸውን ሲጠጡ የሚያሳዩ ፖስተሮችን በማዘጋጀት እንዲሁም በህፃናት መማሪያ መፃህፍት ሳይቀር አይሁዶችን በአይጥ እና በበረሮ በመመሰል ሆሎኮስት ከመፈፀሙ በፊት ትልቅ ከሰውነት ተራ የማስወጣት /Dehumanization/ ስራ ሰርቶባቸው ነበር።

እንዲሁም የሶቭየት ዩኒየኑ ጃሴፍ ስታሊን በ1932 ዓ.ም. አካባቢ የመንደር ምስረታ ፕሮግራም /Villagization/ እና የገበሬዎች የእርሻ ማህበራትን በዩክሬን ተግባራዊ ለማድረግ በተነሳበት ወቅት ከዩክሬን ህዝብ ተቃውሞ ሲገጥመው ይህንን በኃይል ለማስፈፀም ይረዳው ዘንድ አስቀድሞ የዩክሬን ህዝብ በአንደኛው የአለም ጦርነት ወቅት ከጀርመን ጋር ወግኖ ራሺያን ወግቷል የሚል የከሃዲነትን ካባ ከደረበላቸው እና ታሪካቸውን ካጠለሸ በኋላ ዛሬም ድረስ በአሰቃቂነቱ ወደር የሌለውን "ሆሎዶሞር" በመባል የሚታወቀውን ስምንት ሚሊየን ዩክሬናውያንን የቀጠፈውን በረሃብ አለንጋ በጅምላ የመግደል ወንጀል /Weaponization of Hunger/ ፈፅሞባቸዋል።

ዛሬ ይህንን እንድናነሳ ምክንያት የሆነን ወያኔ ትግሬና ግብረአበሮቹ የአማራን ህዝብ "የነፍጠኛው ሥርዓት" መሠረት ነው ብለው ከመፈረጅም በላይ አማራዊ ማንነታችንም ሆነ የምንከተላቸው አበይት እምነቶቻችን፣ ባህላችንም ይሁን የጦርነት ህጎቻችን የማይፈቅዱልንን እና እኛነታችንን ፈፅሞ የማይወክሉ፣ ይልቁንም በእኛ ዘንድ ፀያፍ እና ነውር የሆኑ ታሪካዊም መሠረት የሌላቸውን የሰውን አካል የመስለብ እና የሴቶችን ጡት የመቁረጥን የሐሰት ካባ በታሪካችን ላይ ከመደረብ አልፈው ትውልዶቻቸውን በዚህ አተያይ ለመቅረፅ ይረዳቸው ዘንድ እዚህ እና እዚያ የጥላቻ ሀውልቶችን ማቆምን ስራዬ ብለው ሲያያዙ ስናይ አማራዊው ወገናችን የመጨረሻው መጀመሪያ ላይ እንደደረሰ እና ዛሬ በአማራዊ ማንነታችን ካልተሰባሰብን፤ ብሎም የመደበቂያ ግንብ የሚሆነውን የራሳችንን ሀገር ካልመሰረተን፤ "የተረፉት በሞቱት ይቀናሉ" የሚለውን አባባል እኛም በዘመናችን እንደምንደግመው ከነዚህ ምልክቶች ውጪ ሌላ ነጋሪ ስለማያሻን ነው።

ስለሆነም እነዚህን ፀረ-አማራ ሐውልቶች እና ምልክቶችን በዝርዝር ቀጥለን እንመለከታለን።

**ሀ. የአኖሌ ሐውልት**

ዛሬ የኦሮሞ የዩኒቨርሲቲ እና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በትምህርታዊ ጉብኝት ሽፋን እንዲያዩት ከሚደረጉ ስፍራዎች መካከል ከሁለት ሚሊየን ዶላር በላይ ወጪ የተደረገበት እና በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን በሂጦሳ ወረዳ እ.ኤ.አ. እሁድ ኤፕሪል 06, 2014 ዓ.ም. በርካታ ሺዎች ከየአቅጣጫው ተጠራርተው ያስመረቁት የአኖሌ ሐውልት አንዱ ነው።

ይህ ሐውልት የቆመለት የአኖሌ የጡት ቆረጣ ተረት ተረት አንዳችም የፅሑፍ ማስረጃ የማይገኝለት ሲሆን /የታሪክ ምሁር እና የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ቅዳሜ ሜይ 24, 2014 ዓ.ም. ለታተመው አዲስ አድማስ ጋዜጣ የሰጡትን ቃለ ምልልስ መመልከት ልብ ይሏል!!!/ ይልቁን ከአመታት በፊት በወያኔ ትግሬ ሃሳብ አመንጪነት እንዲሁም በተስፋዬ ገብረ አብ ፀሐፊነት ትናንት በልብ ወለድ መጽሐፍነቱ ያየነው "የቡርቃ ዝምታ" ከህሊናዊ ቅዠትነት ወጥቶ ቁሳዊ-መሠረት ቢይዝ በአማራዊው ደም ኪሳራ ወያኔ ትግሬ ሊያጋብስ የሚችለው ፖለቲካዊ ትርፍ ታስቦ የቆመ የጥላቻ ሀውልት ነው። ዛሬ አኖሌ ዳርዊናዊ የዘገምተኛ ለውጥ ሂደቱን ጨርሶ ከልብ ወለድነት ወደ ሐውልትነት ከመሸጋገሩም በላይ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ስያሜ ከመሆን አልፎ ማጣቀሻ የሌላቸው መጽሐፎች እየተፃፉለት እና"ታሪክ" ቀመስ ፊልሞች እየተሰሩለት ነው።

ይህ ትልቅ የማንቂያ ደወል ተደርጎ በአማራዊው ዘንድ ሊወሰድ ይገባል የሚል እምነት አለን። እስራኤል እንደ ሀገር ከመመስረቷ በፊት ህዝቧ በየሀገሩ ተበትኖ ሳለ ድሬፊዩስ የተባለው አይሁዳዊ የፈረንሳይ ወታደር መረጃ ለእንግሊዝ አሳልፈህ ሰጥተሃል በሚል የፈጠራ ክስ ወታደራዊ ማዕረጉን በአደባባይ ሲገፈፍ እና ሰብዓዊ ክብሩ በአደባባይ ሲዋረድ ያይ የነበረው የወቅቱ ጋዜጠኛ በኋላ ግን የጽዮናውያን እንቅስቃሴ መሪ የነበረው ቲዎዶር ሄርዝል ያቺ ቅጽበት ለአይሁዳውያኑ የማንቂያ ደውል ትሆን ዘንድ ብዙ ይወተውት ነበር። ይሁን እንጂ አብዛኛው አይሁዳዊ እዚህም እዚያም የሚደርስበትን የዘር ጥላቻ እና ማሳደድ እንደ ድንገተኛ ክስተት በአጋጣሚ የሚከሰትና በሂደት የሚቆም እየመሰለው ፍፁም በመዘናጋቱ የናዚ ጦር ከጀርመን አልፎ አውሮፓን ማጥለቅለቅ ሲጀምር እግር በእግር እየተከተለ ነበር መሸሸጊያ እስኪያጡ ድረስ ያጠፋቸው። ዛሬም አንተ አማራዊ ወገናችን

ራስህን በአማራዊነትህ ማደራጀት ካልቻልክ እና ዘለቄታ ያለው ዕረፍት የምታገኝበትን ሀገርህን ለመመስረት ዛሬ ቆርጠህ ካልተነሳህ የጅምላ ሞት በጥላቻ ውስጥ ተደብቆ በየአቅጣጫው ራሱን እንደሱናሚ እያሳደገ ፈጽሞ ሊያጠፋህ እየመጣ ነው።

እነዚህ ሰዎች ለአንተ ለአማራዊው "የአኖሌን ሀውልት የሰራነው አዲሱ ትውልድ እንዲማርበት፥ዳግምም እንዳይከሰት ነው" ይሉሃል፤ በጎን ግን ለዜጎቻቸው "ትናንት ነፍጠኛ አማራ የቀደመ እናቶችህን ጡት ቆረጠ፤ ዛሬ እዚህ በዙሪያህ ያሉ አማራዎች በሙሉ ትናንት ጡት ሲቆርጡ የነበሩት ሰዎች ልጆች ናቸው" እያሉ ጥላቻን ይግቷቸዋል። በመሬት ላይ ያለው ሐቅ ይሄ ነው!!! በቋንቋችን ከሚነግሩን ይልቅ ዘፈኖቻቸው (https://www.youtube.com/watch?v=jl7yWy25IBs መመልከት ልብ ይሏል!!!) እና የትምህርት ቤት የታሪክ መጽሐፎቻቸው እያረጋገጡልን ያለው ሐቅ ይህንኑ ነው!!!

ደግሞም እኮ ሐውልት በማቆም አዲሱን ትውልድ ማስተማር ከተቻለ እንደነሱ በተረት እና በፈጠራ ታሪክ ተመስርቶ ሳይሆን በእውነት ለተፈፀሙ ጭፍጨፋዎች ለምሳሌ ዮሐንስ የተባለው የትግሬ ንጉስ የጎጃም እና የወሎ አማራውያን ላይ የፈፀመውን ግፍ ለማስታወስ፣በበደኖ እና በአርባጉጉ እንዲሁም በአሰቦት እና በበሻሻ፣ በግራኝ አህመድም በተፈፀሙ ዘግናኝ ተግባራት ለተሰዉ ንጹሐን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ዳግምም የዚህ አይነቱ ተግባር እንዳይከሰት ለማድረግ ብዙ ሐውልት የሚገባን እኛ አማራውያን ነበርን። ዳሩ በፈጠራ ታሪክ እና በተረት ተረት ተመርኩዞ ጥላቻን ከመስበክ ውጪ ለትምህርትም ይሁን ለመታሰቢያነት በወያኔ ትግሬም ይሁን በጋሻጃግሬዎቹ የተሰራ ሀውልት የለም።

### ለ. የጨለንቆ ሐውልት

እንዲህም ሆነ። በኢትዮጵያ አቆጣጠር መጋቢት 12፣ 2007 ዓ.ም. ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ሜታ ወረዳ ልዩ ስሙ ጨለንቆ በሚባል ስፍራ ከላይ ጥቁር፥ ከታችም በርገንዲ ቀለም ባለው ልብሥ ያጌጡ፤ ከተነገራቸው ውጪ ከፉውን እና ደጉን በቅጡ ለይተው የማያውቁ በሺህ የሚቆጠሩ ህፃናት "ኢቲን ቦና ዮሚሌ" እያሉ ይዘምራሉ።

እነዚህ ህፃናትን ከል አስለብሶ የሚያዘምራቸው ቢታመሙ የሚታከሙበት ሆስፒታል፥ አልያም የነገ ተስፋቸውን የሚያለመልሙበት ትምህርት ቤት ስለተሰራላቸው አልነበረም። ይልቁን ወያኔ ትግሬ ምርኮኛ ወታደሮችን ሰብስቦ ኦህዴድ የሚል የዳቦ ስም ያወጣለት ድርጅት የተመሠረተበትን ሃያ አምስተኛ አመት ሲያከበር ሌላ በተረት ተረት የተመሰረተ የጥላቻ ሐውልት አቁሞ ከሊቅ እስከ ደቂቅ በመሰብሰብ በአይጋ ፎረሙ ጋዜጠኛ ታምራት የማነ እና መሰል ትግሬዎች አጫፋሪነት ነበር ፀረ-አማራ አስረሽ ምቺው የሚያስደልቀው። በእርግጥም ትናንት የክልሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንደፎከረው ዛሬ ይህ ቦታ እንደ አኖሌ ሁሉ ምልምል ካድሬዎችና ወጣት ተማሪዎች የሚጎበኙት፣ ጥላቻንም የሚጋቱበት "የቱሪስት" መዳረሻ ሆኗል።

በእርግጥ አሁን አሁን የጨለንቆ ጦርነት በተነሳ ቁጥር በታሪክ ሽሚያ ላይ ግብግብ የሚገጥሙ ሁለት የታሪክ እና የተረት እስረኞችን /The Prisoners of History and Myth/ በግላጭ እየታዘብን ነው። በአንድ በኩል ጦርነቱን በዋናነት የተዋጉት እና ድልም የተሙቱት አደሬዎች የራሳቸውን "ተጨፍጭፈናል" የሚል ትርክት ይዘው በሐረር ከተማ "የጨለንቆ አደባባይ" ብለው ሲሰይሙ እና ሀውልት ሲሰሩ በሌላ በኩል አደሬዎችንም ጭምር ከፉኛ ባስደነገጣቸው ሁኔታ የኦሮሞ ልሂቃን እና ኦ.ፒ.ዲ.ኦ ስድስት ሰዓት ብቻ የፈጀችውን ጦርነት በሚሊየን አባዝተው እና እነሱ በዋናነት የተዋጉት ጦርነት አስመስለው ያው የተለመደ "የተጨፍጭፈናል" ነጋሪታቸውን እየጎሰሙ፤ ብሎም ታሪክን ለፖለቲካ ትርፍ በሚያመቻቸው መልኩ በአማራዊው ኪሳራ እየፃፉት ይገኛል።

ኦሮሞዎቹ የጨለንቆን ጦርነት በዋናነት የተዋጉ በማስመሰል ሐውልት ሲያቆሙ እና አይጋ ፎረም የሚባለው የትግሬ ወያኔ ድረ-ገጽ ይህንን ሲያራግብ አደሬዎቹ ለአይጋ ፎረም መልዕክት ከመላክ ጀምሮ የይስተካከልን እርማት እንዲወሰድ እስከመወትወት ደርሰው ነበር / ኻሊድ መሐመድ የተባለ የአደሬ ተወላጅ ቅሬታውን ለአይጋ ፎረም የፃፈበትን መመልከት ልብ ይሏል http://www.aigaforum.com/Archive/ArchiveMar2015-5.htm /

በዚህ ሂደት ውስጥ አማራዊው ልብ ሊለው የሚገባ ነገር ቢኖር እነዚህ ሰዎች ከሊቅ እስከ ደቂቅ፤ ከኦህዴድ እስከ ኦነግ በወያኔ ትግሬ የሀገር ቤቱን መደላድል /Platform/ አመቻቺነት ቀን ከሌሊት እየሰሩበት የሚገኘው ነገር ቢኖር ጥልቅ የሆነ ፀረ-አማራ

ጥላቻን በህዝባቸው ውስጥ ማስረፅ ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ደግሞ የጨለንቆ ሐውልት በተመረቀ ማግስት ቢያንስ እኔ የዚህ ጽሑፍ ፀሐፊ በማውቀው ከአስር በላይ የሚሆኑ አፍቃሬ ኦነግ እና የቄቤው ትውልድ ዘፋኞች በዋናነት ባልዋሉበት የጨለንቆ ጦርነት እና በራሳቸው በፈጠሩት የተረት ተረት ጭፍጨፋ ዙሪያ አማራዊውን ከሰውነት የማውጣት /De-humanization/ ስራ ሰርተዋል፤ እየሰሩም ነው።

አማራዊው ወገናችን ሆይ! አሁንም ደግመን እንልሃለን፡- በቋንቋህ የሚነግሩህን ሳይሆን፥ በቋንቋቸው የሚሉትን በአጽንዖት ስማ!!! ያን ጊዜ ዛሬ በአማራዊነትህ መሰባሰብ ካልጀመርክ፣ ራስህ ነቅተህ ህዝብህንም ካላነቃህና ካልተደራጀህ፥ ፊጥህም አይን ስለአይን፥ ጥርስም ስለጥርስ ማለት ካልጀመርክ ነገ የቆምንበት መሬት ሁሉ እንደሚከዳን ሌላ ነጋሪ አያሻንም። "ይህም ያልፋል፥ ነገ ሌላ ቀን ነው" የማይባል ትልቅ አደጋ ነገ እንደ ህዝብ በመኖር ወይ ባለመኖራችን ላይ ተደቅኗል። አደጋው በእርግጥም እግር እና እጅ፤ ጥፍር እና ጥርስ አውጥቶ ከፊታችን ተጋርጧል። እያለ እንደሌለ ብንረሳው አልያም አቅልለን ብናየው ከእኛ ህሊናዊ ምዘና በተቃራኒ አደጋው ሊያጠፋን እየተንደረደረ ነው። በመንግስት በጀት የሚንቀሳቀሰው "ቢፍቱ ኦሮሚያ" የሚባለው የኪነት ቡድን የሚሰራው ሙዚቃዊ ድራማ እንቅልፍ የሚያስተኛ አይደለም። በመንግስት ይተዳደራል የሚባለው የሚዲያ ተቋም በቋንቋቸው ቂም እና ቁጭትን ጥላቻንም ይሰብካቸዋል፤ ታዳጊዎቻቸው በትምህርት ቤት መዝሙሮች፣በታሪክ እና ስነ-ዜጋ ትምህርቶቻቸው በተመሳሳይ በሐሰት በተቦካ ታሪክ ይሰበካሉ። በመዝናኛ ስፍራዎቻቸው ዘፋኞቻቸው በሚጨፈጭፋቸው እና በሚዘርፋቸው ትግሬ ላይ ሳይሆን በአማራ ህዝብ ላይ ምሬትን እና ጥላቻን ይዘፍናሉ። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ያደገ ሰው ነገ አይደለም አብረነው ልንኖር መልካም ጎረቤት ለመሆን እንኳን እጅግ ይቸግራል።የቀረን አንድ አማራጭ ብቻ ነው። ይኸውም እውነታውን እንዳለ መቀበል። ይህን እውነት እንዳለ ሳንሸራርፍ እና ሳንቀባባ ስንቀበል ደግሞ በአማራዊነታችን ብቻ መሰባሰብ ካልቻልን መጪው ጊዜ የእኛ እንዳልሆነ ፍንትው ብሎ ይታየናል።

**ሐ. የአደሬ የጥላቻ ልብስ**

የቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ በመበታተኛዋ ዋዜማ ልክ ዛሬ ኢትዮጵያ እንዳለችበት ሁኔታ በውስጧ ይኖሩ የነበሩ ሰርቦች፣ ክሮአቶች፣ ቦስኒያውያን፣ መሴዶናውያን እና አልባንያውያን በታሪክ ላይ ትልቅ ሽሚያ ያደርጉ ነበር። የሁሉም ሽሚያ "ተበድለናል" የሚል ታሪክ ለማፃፍ የሚደረግ ሩጫ ነበር። እርግጥ ነው ከኢትዮጵያው ሁኔታ የሚለየው በዩጎዝላቪያ እንደበዳይ የሚወሰድ አንድ ህዝብ ብቻ አልነበረም።

አደሬዎች በባህላቸው መሠረት ለሙሽራ በጥሎሽ ከሚሰጡት ስጦታ መካከል ቀይ ጥለት ያለው ጋቢ አንዱ ነው።ይህን ባህላቸውን በኃይለ ሥላሴም ይሁን በደርግ ዘመን ሲተገብሩት ኖረዋል። ወያኔ ትግሬ አዲስ አበባ ሲገባ እና ነፃ አውጪ ነኝ ባዩ ሁሉ በአማራ ህዝብ ላይ የጥላቻ ዶፉን ማዝነብ ሲጀምር አደሬዎችም ይህን ቀይ ጥለት ጋቢ "በጨለንቆ ጦርነት ለተገደሉ 700 ሙሽሮች" መታሰቢያ እንዲሆን በጥሎሽ የምንሰጠው ስጦታ ነው ሲሉ አይናቸውን በጨው ታጥበው ብቅ አሉ። ለመሆኑ በዚያች የስድስት ሰዓት ጦርነት 700 ሙሽራ ተገደሏል ወይ?ይህን ጥያቄ ለመመለስ በጨለንቆ ጦርነት እንዲሁም በምኒልክ ህይወት ዙሪያ ሃሮልድ ማርከስ የፃፈውን The Life and Times of Menelik II: Ethiopia 1844-1913 የሚለውን መፅሐፍ መጥቀስ ሳያስፈልገን የራሳቸው የሐረሪ ተወላጅ የሆኑት ሼህ አህመድ መሐመድ ኪቦ አል ሐረሪ "ስለ ጨለንቆ ጦርነት አጭር ታሪክ" በሚል ባሳተሙት ጽሑፍ ላይ አንድም ቦታ ተገደሉ ስለተባሉት 700 ሙሽሮች ተረት ያልፃፉ ሲሆን ይልቁን እኒህ ሰው ጦርነቱ ከተካሄደ በኋላ "ሙአህደቱል ጨለንቆ" ወይም "የጨለንቆ ውል" ከሚል በንጉስ ምኒልክ እና በአሚር አብዱላሂ አንት መካከል የሐረር ከተማን ለምኒልክ ለማስረከብ በተደረገ ጥንታዊ የውል ሰነድ ላይ ያገኙትን የውል ስምምነቶች ያሰፈሩ ሲሆን ምኒልክ የገቡትን ቃል ሲያሰፍሩም፡-

1. "የሐረሪ ህዝብ እምነቱና ባህሉ ተጠብቆለት በሰላም እንዲኖር፤
2. "ማንኛውም ሰው የሐረሪ ጉዳይ ብሎ እንዳይፎክር፤"
3. "የሐረሪ ተወላጅ የሆነ ማንኛውም ሰው በጅራፍ እንዳይገረፍ፤"
4. "ማንኛውም የሐረሪ ተወላጅ የሆነ ሰው የጉልበት ሥራ እንዲሰራ እንዳይገደድ"

የሚል ሲሆን እኒሁ ሰው እንዲህ ሲሉ ፅፈዋል፡- "የሐረር መንግስት በጦር ሜዳ ቢሸነፍም ባንድ ተሸናፊ ሕዝብ ላይ ይደርስ ከነበረው ለባሪያነት ውርደት ሳይዳረግ እምነቱንና ክብሩን ጠብቆ በሰላም ለመቆየት ችሏል፡"

ታዲያ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ እነዚህ የሰባት መቶ ሙሽሮችን የመገደል ተረት የሚያወሩትን ሰዎች አጥብቃችሁ ስትጠይቋቸው የሚሰጧችሁ መልስ ይህን ይመስላል፡- "ወደ ጨለንቆ /ከሐረር 70 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የሚገኝ ስፍራ ነው/ ለጦርነት ከወጡት የአደሬ ወታደሮች መካከል ሰባት መቶ ያህሉ ጦርነቱ በተካሄደበት ዓመት ያገቡ ወታደሮች ናቸው" ይላሉ። መቼም የሚሉት ተረት እውነት ነው ቢባል እንኳ እነዚህ ሰዎች መሳሪያ ታጥቀው ወደ ጦር ግንባር የዘመቱት ለጫጉላ ሽርሽር ሳይሆን ቢችሉ ገድለው ድልን ለመቀዳጀት ነው። ደግሞስ በውጊያ መሐል አንተ አዲስ ሙሽራ ነህ፣አንተ ደግሞ እንዲያ ነህ የሚባል ነገር አለ ወይ?

እነዚህ ሰዎች ልክ እንደ ኦሮሞዎች ሁሉ የጨለንቆን አደባባይ እና ሐውልት በሐረር ከተማ ሲያስመርቁ የሰባት መቶ ሙሽሮችን የተረት ተረት ጭፍጨፋ ማህበራዊ መሠረት ለማስያዝ በማሰብ በዕለቱ አርባ /40/ ጥንዶችን አጋብተዋል። /http://saayharari.com/pages/news.asp?id=13 መመልከት ልብ ይሏል!/

በዚህ አጋጣሚ በክፍል አራት ላይ በሐረር የሚኖሩ አማራውያን ላይ በነዚህ ሰዎች እየደረሰባቸው ያለውን ግፍ እና በደል በከፊል ማየታችንን ለማስታወስ እንወዳለን።

### ሠ.2.1.2. ሙዚቃ (ዘፈን) /Absorbing High Culture Tactic/፡-

ደግሞም እንደዚህ ሆነ። የቴሌቪዥን ካሜራዎች እና ፓውዛ መብራቶች ፊታቸው በእንባ ጎርፍ ይታጠብ ወደነበረው የወቅቱ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት ሙክታር ከድር፣ የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ኃላፊ በነበረው ዳባ ደበሌ፣ የጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ዳይሬክተር በነበረው በከር ሻሌ እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚንስትሯ ደሚቱ ሃንቢሳ ላይ አነጣጥረው ይቀርፃሉ። እ.አ.አ ኦገስት 23, 2015 ዓ.ም. የኦ.ህ.ዴ.ድ 8ኛ መደበኛ ጉባኤ በናዝሬት ከተማ "አባ ገዳ አዳራሽ" ከአንድ ሺህ በላይ ሰዎች በተገኙበት ሲከፈት ነበር "ቢፍቱ ኦሮሚያ" የተባለው የኪነት ቡድን ከዘጠና በላይ አባላቱን አሳትፎ በመርዝ የተለወሰ ፀረ-አማራ ሙዚቃዊ ድራማውን ያቀረበው። ይህ ከትላልቅ ባለስልጣናት እስከ ግልገል ካድሬ ድረስ ያነፈረቀበት ሙዚቃዊ ድራማ አጠቃላይ ጭብጡ፡-

- "የአማራ ህዝብ የገዳ ስርዓትን ያጠፋበት መንገድ"፣
- "በአኖሌ እና በጨለንቆ የአማራ ህዝብ በአሰቃቂ ሁኔታ ኦሮሞዎችን ሲጨፈጭፍ"፣
- "የአማራ ህዝብ የኦሮሞ ወንዶችን ብልት /እጅ አይደለም ያልኩት። ያቀረቡት አማራ ብልት ሰልቧል ብለው ነው!/ እና የኦሮሞ ሴቶችን ጡት ሲቆርጥ"፣
- "እንዲሁም የአማራ ህዝብ የኦሮሞ ህዝብ በኢኮኖሚው ተጠቃሚ እንዳይሆን ያደረሰው በደል.........ወዘተ" የሚል የፈጠራ ክስ ነበር።

ይህ ሙዚቃዊ ድራማ "በአባ ገዳ አዳራሽ" መድረክ ብቻ ሳይወሰን "ቲቪ-ኦሮሚያ" በሚባለው መንግስታዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ አማካኝነት ለመላው ህዝባቸው ደግመው ደጋግመው በማሳየት ፀረ-አማራ ጥላቻን በመንግስት ደረጃ አስርፀውበታል። ባለስልጣናቱም የታሰበውን ፀረ-አማራ ጥላቻ በህዝባቸው ልቦና ለማስረፅ ይረዳቸው ዘንድ ስሜት በሚኮረኩር መልኩ /Appeal to Emotion/ ካሜራው መድረኩን እና የሚያለቅሱትን ባለስልጣናት ፊት በየተራ እንዲያሳይ በተቀናጀ እና በተጠና ሁኔታ ተውነውታል።

የኦሮሞ ሙዚቀኞች ስራዬ ብለው የተያያዙትን የአማራ ጥላቻን የማስረፅ ዘመቻ ስንፈትሽ ቀድሞ ወደ ህሊናችን የሚመጣው በሩዋንዳው የቱትሲዎች የዘር ፍጅት ላይ ሙዚቃን እንደ አንድ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ በመጠቀም ጥላቻን ሲያራግብ የነበረው እና ከበርካታ የጥላቻ ዘፈኖቹ መካከል "ቤኔ ሲቢሂንዚ" እያለ የሚያቀነቅነው ሳይመን ቢኪንዲ ነው። ከዘር ፍጅት ጭፍጨፋው

በኋላ በርካታ ሁቱዎች በሬድዮ ሚሌ በተደጋጋሚ ይተላለፉ የነበሩ የሳይመን ቢኪንዲ ዘፈኖች ልቦናቸውን እንዳሸፈተው ገልፀዋል።

በተመሳሳይ የኦሮሞ ሳይመን ቢኪንዲዎች ትናንት በነ አብተው ከበደ ቀረርቶ፣ በነ ኡስማዮ ሙሳ "ሴና ዳባ" በሚለው ዘፈናቸው እንዲሁም በነ ኤቢሳ አዱኛ "ናን ዲዲኒ ዱቢ ቲያ" ዘፈን ሲራገብ የነበረው የፀረ-አማራ ዘፈን ዛሬ ብዙ የኦሮሞ ሳይመን ቢኪንዲዎችን አፍርቶ ከሰርግ እስከ መንግስታዊ ስብሰባዎች፤ ከጭፈራ ቤቶች እስከ ህዝብ ማመላለሻ መኪናዎች በነዚህ ፀረ አማራ ዘፈኖች ይደምቃሉ።

እንዲሁ በወፍ በረር ብንቃኝ እንኳን ባለፉት አራት እና አምስት አመታት ውስጥ የሚከተሉት የኦሮሞ ሳይመን ቢኪንዲዎች ፀረ-አማራ ጥላቻቸውን በዘፈኖቻቸው አሰራጭተዋል፡-

- ኢብሮ መሐመድ "ኢያዱ ያ ዳቺ" በሚለው ዘፈኑ፣
- ኤለሞ አሊ "ምኒልክ ጄኖሳይድ" በሚለው ዘፈኑ፣
- ሹክሪ ጀማል "ምኒልክ ኑፊ ዲና" በሚለው ዘፈኑ፣
- ከድር ማርቱ "አስ ኮቱ" በሚለው ዘፈኑ፣
- ቢፍቱ ያሚ "ያ ጨለንቆ ጫሊ" በሚለው ዘፈኗ፣
- አሊ ሳቢት "ላፊሌ ጨለንቆ" በሚለው ዘፈኑ እንዲሁም
- ቀመር የሱፍ "ኢያ ደበርሳ" በሚለው ዘፈኑ ሲሆን ይህ የወያኔ ፍርፋሪ ለቃሚ ዘፋኝ የሌሎችን ብሔሮች ስም እየጠራ "አይዟችሁ ተነሱ" እያለ በአማራዊው ላይ የማነሳሳት ስራ ሰርቷል።

ዛሬ እኮ አብዛኛው የኦሮሞ ተወላጅ ወያኔ ትግሬ እየገደለው አማራን ስር በሰደደ ጥላቻ የሚጠላው ቀን ከሌሊት ቦታ ሳይመርጥ በእያንዳንዱ ቤት በሚገኘው የጥላቻ ሙዚቃ እና የቴሌቪዥን ድራማዎች ተፅዕኖ ጭምር ነው።

አማራዊው ወገናችን ሆይ! አሁንም ለሦስተኛ ጊዜ እንልሃለን፡- በቋንቋችን የሚሉትን ሳይሆን፥ በቋንቋቸው የሚናገሩትን በአፅንኦት አዳምጥ። ያኔ እንዴት ባለ አደጋ እንደተከበብን ትረዳለህ። ታዲያ ሊመጣ ግድ ከሆነው ከዚህ አደጋ መትረፍ የምንችልበት ዕድል አንድ ነው፤ ይኸውም በአማራዊነታችን በንቃት መሰባሰብ እና ለዘለቄታው የሚሆነውን አባታዊ ሀገራችንን በታሪካዊ ይዞታዎቻችን ላይ መመስረት መቻል ነው!!!

ሡ.2.1.2. የልሂቃን ቅጥፈት /Misrepresentation of Fact and History by Scholars /፡-

.

.

>>>>>>>>ይቀጥላል<<<<<<<<

የአማራ ብሔርተኝነት ይለምልም!!!

ቸር እንሰንብት!
ዴቭ ዳዊት።